ልዩ ዕትም

# ስምዐ ጽድቅ

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

«የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውን እንመሰክራለን»

፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፲፯/ ቅጽ ፲፰ ቁጥር ፪፻፷፭ ከግንቦት ፲፮ - ፴ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም web-site. http//www.eotc-Mkidusan.org ዋጋ 4.00

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ»
/ሐዋ.፳፥፳፰-፴/

# ቅዱስ ሲኖዶስ



የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ

ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት /ኤጲስ ቆጶሳት/ የሚያደርጉት የቅድስት ቤተክርስቲያን ዐቢይ ጉባኤ ነው። /ሕገ ቤተክርስቲያን ፲፱፻፺፩/። የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ መሪው መንፈስ ቅዱስ የሆነ፣ የቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ የሥልጣን ባለቤት ነው። የሚመራው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ለማመልከት ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲያደርግ የመካከለኛው ወንበር ክፍት ተትቶ ቅዱስ ወንጌል ይቀመጥበታል። /ፍት.ነገ.አንቀጽ ፫ ቁ ፩፻፳፫/። የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፓትርያርኩ ሰብሳቢነት ይካሔዳል። ቅዱስ ሲኖዶስ የሚወስነው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

ቤተክርስቲያንን በበላይነት ይመራል፤ ይጠብቃል። ቀኖናዎችን፣ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል፤ ያሻሽላል። የቤተ ክርስቲያኒቱን የአስተዳደር መዋቅር፣ የአገልግሎት ዘርፎችንና ጽ/ቤቶችን ምንነትና ደረጃ እንዲሁም ተጠሪነቱን ይወስናል። ኤጲስ ቆጶሳትን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በምልዓተ ጉባኤ ይሾማል።

### ይህ የቅድስት ቤተክርስቲያን የመጨረሻው የሥልጣን ባለቤት የሆነ ዐቢይ ጉባኤ መሠረት ምንድነው?

ሲኖዶስ ቃሉ ከግሪክ ልሳን የተገኘ ነው። ሲን-ኖዶስ ማለትም፣ አንድነት፣ ኅብረት፣ ጉባኤ ማለት ነው።

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል።

## ቅዱስ ሲኖዶስ ጠንካራ ውሳኔ ያሳልፋል ተብሎ ይጠበቃል

በቤተክርስቲያኒቱ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ የሚመክረው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በቀጣይ በቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት መጠናከርና በገጠሟት ችግሮች ላይ መፍትሔን የሚሰጥ ጠን ካራ ውሳኔ ያሳልፋል ብሎ እንደሚያምን ማኅበረ ቅዱሳን አስታወቀ።

የማኅበሩ ሰብሳቢ ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ ሥዩም እንዳስታወቁት፤ ዘን ድሮ ከግንቦት ፲ ቀን ጀምሮ የሚካሔደው ዓመታዊ መደበኛ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በእግዚአብሔር አጋዥነት እና በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ በመሆኑ ጠቃሚ አሳቦች የሚነሡበት፤ ለቅድስት ቤተክርስቲያን የሚበጁ ጠንካራ ውሳኔ ዎች የሚተላለፉበት እንደሚሆን ማኅበረ ቅዱሳን በፅኑ ያምናል።

«በቅድስት ቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለው ቦታና ልዕልና ከፍተኛ ነው፤ ስለዚህም የቤተክርስቲያኒቱን ዶግማና ቀኖና ከማስጠበቅ፣ በየጊዜው የሚያጋጥሟትን ችግሮችና ፈተናዎች ላይ ውሳኔዎችን ከማሳለፍ አንፃር የጉባኤው ውጤት በጉጉት ይጠበቃል» ያሉት ሰብሳቢው፤ ይህ ይሆን ዘንድ ማኅበሩ ምኞቱን ይገልጣል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት የቤተክርስቲያኒቱን ሥርዓት፣ዶግማ እና ቀኖናዋን እንዲ ሁም ማንነቷን የሚሸረሽር ትልቅ የተሐድሶ እንቅስቃሴ መኖሩን የጠቆሙት ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ፤ በዚህ ላይ የሲኖዶሱ ውሳኔ ወቅታዊነት ያለው ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

በፀረ ቤተክርስቲያን ኃይሎች መንፈሳዊ ተቋማትና ገዳማትን የመ በረዝ፣ ውስጧንም የመቀየርና ማንነቷን የማጥፋት ሰፊ ሥራ እየሠሩ መሆኑን ጠቅሰው በእነዚህና በመሳሰሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ እንቅፋቶች ላይ ጉባኤው መክሮ የሚያሳልፈው ውሳኔ ጠቃሚ እና ተስፋ ሰጪ እንደሚሆንም እምነታ ቸውን ገልጠዋል።

ውሳኔውን ተከትሎ ለማስፈፀ ሚያነት የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን በአግባቡ የመከታተልና የመቆጣጠር ሓላፊነትም የቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑን ጠቅሰው፤ አፈጻጸሙ ላይ ማኅበሩ የቤተክርስቲያኒቱ አካል እንደመሆኑ መጠን የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።



ቀሲስ ዶክተር ሙሉጌታ ሥዩም
የማኅበረ ቅዱሳን ሰብሳቢ

እንደ ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ ሥዩም ገለጻ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔዎችን እንደ ቅድስት ቤተክርስቲያን አካልነቱ ከመፈጸም እና ከማስፈጸም በተጨማሪ ማኅበሩ ባለው የኅትመት ውጤቶች ማለትም በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ፣ በሐመር መጽሔት እና በሌሎች የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ለምእመናን የማድረስ ሓላፊነቱን ይወጣል።

ማኅበሩ በቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያና ደንብ መሠረት የተዋቀረ በመሆኑ ለቤተክርስቲያኒቱ ያለውን አጋዥነት አሁንም በተግባር ማረጋገጡን እንደሚ ቀጥል የጠቀሱት ቀሲስ ዶ/ር ሙሉጌታ በአባቶች ምክር፣ ምርቃትና ቡራኬ የሚመራ መሆኑ አገልግሎቱን እንዳገዘው ተናግረዋል። የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ዎችን የማኅበሩ አባላትም ሆኑ ምእመናን አክብረው ተግባራዊ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።✞

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሐድሶ እንቅስቃሴ አለን? ዓላማውና ስልቱስ ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን *"መታደስ አለባት"* የሚሉ ድምፆችን የሚያሰሙ አካላት አሳባቸውን በተለያዩ መንገዶች ማሰማት ከጀመሩ ውለው አድረዋል፡፡ እነዚህ አካላት በመጽሔቶች፣ በጋዜጦች፣ በመጻሕፍት፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በዓውደ ምሕረት ስብከቶችና በሚያገኟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ይኸን ጩኸታቸውን ማስተጋባቱን ተያይዘውታል፡፡ እንዲህ እያሉ ያሉትም *"ኦርቶዶክሳውያን ነን"* እያሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በተለያየ ቦታና ሓላፊነት ላይ ካሉና እንጀራዋን ከሚበሉ፣ ጥቂቶች እንዲሁም ደግሞ በኅቡዕና በግልጽ በተለያየ መልክና ቅርጽ ራሳቸውን አደራጅተው ቤተ ክርስቲያኗ ሳትወክላቸው እርሷን ወክለው፣ "እኛም ኦርቶዶክስ ነን" በሚል ካባ ራሳቸውን ደብቀው እምነቷንና ሥርዓቷን "ይህ ሳይሆን ሌላ ነበር" እያሉ ፕሮቴስታንታዊ ትምህርትና መንፈስ የተዋረሳቸው ሰዎች ናቸው፡፡

> *" ... በዚህ የተቀናጀ ስልት መንፈሳ ዊው ጦርነት ቢቀጥል በውስጥ የተሰለፈው ሠራዊት (በተሐድሶ ስም የሚሠራው የፕሮቴ ስታንት ክንፍ) እያጠቃ ወደ ውጪ ሲገሰግስ፣ በውጭ ያለውም (በግልጽ ፕሮቴስታንት ሆኖ የሚሠራው) ከበባውን አጠናክሮ ወደ ውስጥ ሲገፋ እግዚአብሔር በወሰነው ቀን የውስጡና የውጪው ሠራዊት ሲገናኙ በውስጧ የመሸገው ጠላት መሸነፉን በሚመለከት በአንድነት የድል ዝማሬ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡"*

### ተሐድሶ የሚባል ነገር አለን?

እነዚህ አካላት በአንድ በኩል ተሐድሶ የሚባል ነገር እንደሌለና ተሐድሶ የሚባለው ጉዳይ የሆነ አካል (እነርሱ እንደሚሉት ማኅበረ ቅዱሳን) ስም ለማጥፋት ሲል የፈጠረው የፈጠራ ወሬ እንጂ በሕይወት የሌለ ምናባዊ ነገር እንደ ሆነ ያስወራሉ፣ ይናገራሉ፡፡ ግን በእውነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማዋ፣ ቀኖናዋና ትውፊቷ መታደስ አለበት በማለት የሚሠራ የተሐድሶ እቅስቃሴ የለምን?

ይህን ጉዳይ እነርሱው በይፋ ካወጧቸው የኅትመት ውጤቶቻቸው ለመመልከትና ለመታዘብ ይረዳ ዘንድ ራሳቸው በተለያዩ መጻሕፍቶቻቸው፣ መጽሔቶቻቸውና ጋዜጦቻቸው ካወጧቸው መካከል የተወሰኑትን ብቻ እንመልከት፡-

"እንደ እውነቱ ከሆነ በወንጌል እውነት ከታደሱ በኋላ በየጊዜው እየተመዘዙ የወጡት ምእመናኖቿና አገልጋዮቿ በውስጧ ቆይተው *የተሐድሶን* ሥራ እንዲሠሩ ቢደረግ ኖሮ፣ በወንጌል ተሐድሶ ያገኙ ክርስቲያኖች ለዓመታት የጸለዩበትንና የጓጉለትን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በቅርብ ጊዜ ሊያዩ ይችሉ እንደ ነበር የሚያምኑ ጥቂቶች አይደሉም፡፡" (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 15)

"ተሐድሶ እንቅስቃሴ በመሆኑ፣ እንቅስቃሴም ውጤታማና ትርፉማ ይሆን ዘንድ ዓላማን፣ ሒደትንና ግብን የያዘ ድርጊት እየተከናወነበት ያለ ሊሆን ስለሚገባው፣ ያለፈውና እየሆነ ያለው ግብረ ተሐድሶ ተመዝግቦ ለአሁኑና ለሚመጣው ትውልድ በሥነ ጽሑፍ ዳብሮና አምሮ ሊቀርብለት ይገባዋል፡፡" (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 17)

"በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተን ዐረሞችን በገሀድ ካልነቀልን ተሐድሶን እንዴት ልናመጣ እንችላለን? መባሉ አይቀርም፡፡ ዳሩ ግን ስሕተቶችን ፊት ለፊት ሳይቃወሙ ስሕተቶች እንዲታረሙ ማድረግ የሚቻልባቸው የተፈተኑ መንገዶች አሉ፡፡ ለምሳሌም ..." (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002፣ ገጽ 19)

"ከ2000 ዘመናት በላይ ያስቆጠረች የእኛ ቤተ ክርስቲያንማ እንዴት አብልጦ ተሐድሶ (መታደስ) አያስፈልጋት?" (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2002፣ ገጽ 15)

"ቤተ ክርስቲያናችን በክፉ ሰዎች ሴራ ዓላማዋን ስታለች፣ የሐዋርያትንም ትምህርት ገፍታለች፣ ስለ ሆነም ይህን የሐዋርያት ትምህርት በክፉዎች ምክንያት በመጣሱ በድፍረት ተሳስተሻልና ታረሚ ልንላት፣ በድፍረትም በሥልጣንም ሕዝቡን ልናስተምር ይገባል፡፡" (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2002፣ ገጽ 20)

"ቤተ ክርስቲያናችን በየሀገሩ የተነሣውን የተሐድሶ የወንጌል እሳት በተለይ በሐረር፣ በባሕር ዳር፣ በአዲስ አበባ፣ በማርቆስ፣ በጎንደር፣ በሰሜን ሸዋ፣ በወሎ፣ በትግራይ፣ በባሌ ለማዳፈን ያን ሁሉ እልፍ አእላፍ ሠራዊት የቤተ ክርስቲያን አለኝታ ወጣት ወንጌል ባልገባቸው ምእመናንና ካህናት እያስደበደበች ለሌላ ድርጅት አሳልፋ ከመስጠት ይልቅ ስሕተቷን አርማ ልጆቿን በጉያዋ ብትይዝ ኖሮ ዛሬም ጭምር ጋብ ላላለው ፍጥጫ አትዳረግም ነበር፡፡" (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2002፣ ገጽ 16)

"ሕዝባችን በልማድና በባህል ሃይማኖትን መያዙና ይህን *የያዘውን ሃይማኖት ለመጣልና ለማጣራትም በቂ እውቀት ስለሚጎድለው* በራሱ አንብቦ መረዳት ስለማይችል ..." (የሚያሳውቁት ሃይማኖትን ለማስጣል ነው ማለት ነው) (ይነጋል፣ 1997፣ ገጽ 144)

> **እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችና አባቶች እንደ እንጀራ ልጆች እየተቆጠሩና እየተገፉ እነዚህ ተሐድሶዎች ደግሞ ባለሚሎች መስለው ከዚያም አልፎ ለጽጽስና ታጭተው ማየትና መስማት በእጅጉ ያማል፣ ልብንም ያደማል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች አናት ላይ ወጥተው የጵጵስና መዓርግ ጨብጠው ከመጡ በኋላ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ሊያመጡ ያሰቡትን ስልታዊ አደጋ መገመት ውኃን የመጠጣት ያህል ቀላል ነው፡፡**

እነዚህ እነርሱው ከጻፏቸውና አሳትመው ካሰራጯቸው መካከል ለአብነት ያህል የተጠቀሱት በግልጽ የሚያሳዩን ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትምህርት የሚቃወሙና ሊለወጥ ይገባል የሚሉ ራሳቸውን *"ተሐድሶ"* የሚል ስያሜ ሰጥተው በተለየ መልክና ቅርጽ በግልጽና በኅቡዕ እየሠሩ ያሉ አካላት መኖራቸውን ነው፡፡ ራሳቸው እንዲህ በይፋ "እኛ አለን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል" እያሉ እየተናገሩ "አይ፣ ተሐድሶ የሚባል ነገር የለም" ማለት እንዴት ይቻላል?

### ዓላማቸው ምንድን ነው?

ተሐድሶዎች ዋና ዓላማቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት በመለወጥ ፕሮቴስታንታዊ ይዘት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ምዕራባውያን ሚሲዮናውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አጥፍቶ ፕሮቴስታንታዊ ለማድረግ መሥራት ከጀመሩበት ከሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ሦስት ስልቶችን ተጠቅመዋል፡፡ የመጀመሪያው እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ የሠሩበት ስልት ሲሆን እርሱም የራሳቸውን አስተምህሮ ማስተማር ነበር፡፡ ከ1950 ዓመት ጀምሮ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የሠሩት የራሳቸውን እምነት በመሰበክ ሳይሆን በዋናነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍና በማጥላላት ምእመኑ እንዲኮበልል በማድረግ ነበር፡፡

ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን እየሠሩበት ያለው ሦስተኛው ስልት ደግሞ "ኦርቶዶክስ ነኝ" ብሎ ውስጧ ገብቶ "ትታደስ" እያሉ በመጮኸ ቤተ ክርስቲያኗ እንዳለች እንድ ትለወጥ በማድረግ ምእመናኗን ከእነ ሕንፃዋና አስተዳደራዊ መዋቅሯ መረከብ ነው፡፡ የእነርሱ ምኞትና ዕቅድ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሦስተኛው ሺሕ እንዳትሻገር ማድረግ ነበር፡፡ ነገር ግን እንዳሰቡት አልሆነም፡፡ በዚህም ብስጭታቸውን በተለያዩ ሚዲያዎች ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌም ፓውል ባሊስኪ (Paul Balisky) የተባለ "የዓለም አቀፍ ተልእኮ ማኅበር" የኢትዮጵያ ዳይሬክተር በ1992 ዓ.ም በወጣው "የክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር" በተባለ መጽሔት በሰጠው ቃለ መጠይቅ የደከሙት ድካምና ያወጡት ገንዘብ ሁሉ ወደ ጠበቁት ግብ እንዳ ላደረሳቸው፡-

*"ይህ ሁሉ ጥረት ቢደረግም ወንጌላውያኑ አሁን በማደግ ላይና በመካከለኛ ኑሮ ላይ ያለውን የከተማውን ኅብረተሰብ መቀየር አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም የተማረና ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ከፍተኛ ቅንዓት ያለው የወጣቶች ኃይል ማኅበረ ቅዱሳን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሃያ አንደኛው መ/ክ/ዘመን ዘልቃ መኀዝ ትችል ዘንድ እየተጋደለ ነውና፡፡"*

በማለት ከሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በፊት የማጥፋት ሕልም እንደ ነበራቸው ገልጸዋል፡፡

(The Christian Science Monitor, 8 June, 2000)

ስለሆነም ከዚያ በፊት ያደርጉት እንደ ነበረው በውጭ ሆኖ ምእመናንን ለመንጠቅ በመሥራት ብቻ ካሰቡት ቤተ ክርስቲያኒቱን ሙሉ በሙሉ የማጥፋት ግብ ለመድረስ

ወደ ገጽ ፬ ዞሯል፡፡

# መልእክተ ስምዐ ጽድቅ

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ**

# የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ፤ ዐለትን የሚሰነጥቅ መዶሻ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከቻለችበት ከ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ጀምሮ በመደበኛነት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስን ምልዓተ ጉባኤ ታደርጋለች፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስም የቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪና ሕግ አውጪ አካል በመሆኑ ባለፉት ዘመናት መልካም ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ መመሪያዎችንም አውጥቷል፡፡ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሁሉም አካላት በመመሪያውና በውሳኔው መሠረት ሙሉ ለሙሉ እየፈፀሙ ነው ባይባልም፤ ቤተ ክርስቲያናችንን አሁን ያለችበት ደረጃ ላይ አድርሰዋታል፡፡ በዚህ ወሳኝ ወቅት ከቅዱስ ሲኖዶስ ብዙ የሚጠበቅ ነው፡፡

ሥልጣኔና ዘመናዊነት በበረታበት በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ላይ ብዙ ፈተናዎች ይከሰታሉ፡፡ በቅዱስ ሲኖዶስ የምትመራው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በዓለም ላይ ያለች በመሆኗ በዘመኑ የመጡ ፈተናዎችና ችግሮች ሁሉ ይጋረጡባታል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለአደራው አካል ቅዱስ ሲኖዶስ በመሆኑ በዙሪያው ያሉትን ሁኔታዎች በማጥናት፣ የአፈጻጸም ጉድለቶችን በመለየት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደፊት ሊያራምዱ የሚችሉ ውሳኔዎችን በመወሰን መመሪያ እንደሚያስተላልፉ ይጠበቃል፡፡ በተለይም በአሁኑ ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ በርካታ ችግሮች እየተከሰቱ በመሆናቸው የሚከተሉት ጉዳዮች አንገብጋቢና የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡

### ፩/ ሰንበት ት/ቤቶችና መንፈሳዊ ማኅበራት

ሓላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑና አፈጻጸማቸው ምን ላይ እንደሆነ መታየትና መፈተሽ አለበት፡፡ ሊቆጣጠርና ሊመራ የሚችለው አካል ተገቢው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ሆኖ እንዲመራ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ተከታዩን ትውልድ ልታጣ እንደምትችል መገመት አያስቸግርም፡፡ በመሆኑም የሰንበት ት/ቤቶች ጉዳይ በቸልታ ሳይሆን ልዩ ትኩረት የሚያሻው ተቋም ነው፡፡

### ፪/ ተሐድሶን በተመለከተ

በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያንን እየፈተናት የሚገኘው የውጭ ጠላት ሳይሆን በውጭ ተገዝቶ ወደ ውስጥ የሰረገው የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ ጉዳይ ነው፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ሥርዓትና ቀኖና አዲስ ሕግ እንዲያወጣ የሚጠበቅ ባይሆንም የነበረው ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮና ሥርዓትም እንዳይጣስ ጥብቅ መመሪያ በመስጠት አቅጣጫ ሊያሲዝ ይገባል፡፡ በየቦታው የሚሰጡ መንፈሳዊ ትምህርቶች፣ የሚዘመሩ መዝሙሮች፣ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ያላዩትና ያልመረመሩት በየጓዳው የሚጻፉ መጻሕፍት፣ ወዘተ ተፈትሸው ሥርዓት እንዲይዙ መደረግ አለበት፡፡

### ፫/ ሹመትን በተመለከተ፡-

በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የተከበረና ቅዱስ በመሆኑ ስለ ሚሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት የመጀመሪያው ተጠያቂ በመሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለሢመት የሚቀርቡ እጩዎች በሙሉ ከመንፈሳዊነታቸው በተጨማሪ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፣ የተመሰከረላቸው፣ ብቃት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ዓመት ለመሾም ሳይሆን ለወደፊቱ እጩዎችን ለማግኘትና ለማዘጋጀት ከወዲሁ መወሰን አለበት፡፡ ወቅቱ በተሐድሶዎች አማካይነት ግርግር የበዛበትና ለሰርጎ ገቦች አመቺ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል እንላለን፡፡

### ፬/ መዋቅራዊ አሠራርን መጠበቅ፡-

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሠራር በአብዛኛው ወቅቱ በሚጠይቀው ሒደት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ዘመናዊ ባለመሆኑ ግልጽ የሆነ የሓላፊነትና የተጠያቂነት ይዘት አይታይበትም፡፡ በመዋቅር ውስጥ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ አብረው ያሉት ግለሰቦችም ጭምር በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ ገብተው የራሳቸውን ዓላማ እንዲያራምዱ መንገድ ከፍቶላቸዋል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱን አሠራርና አደረጃጀት በተመለከተ የሚያጠና የባለሙያዎች አካል በማቋቋም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናና እንዲወሰን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### ፭/ ነጋ አድራሶችን እና አጭበርባሪዎችን በተመለከተ፡-

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በመንበረ ፓትርያርክ አካባቢ አንዳንድ ግለሰቦች ወሬ በማመላለስና በማጭበርበር ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ግለሰቦች የአባቶቻችንን የዋህነት እንደጸጋ ቆጥረው ከእግራቸው ሥር በመውደቅ በረከት ማግኘት ሲገባቸው የተጭበረበሩ የሐሰት ሰነዶችን በማቅረብ የቤተ ክርስቲያን አካላት እርስ በራሳቸው እንዲጋጩ፣ አባቶች ልጆቻቸውን እንዲጠሉ፣ ልጆች በአባቶቻቸው ላይ ጥርጣሬ እንዲኖራቸው እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ዋና ማሳያ የሚሆነው በሐሰት በማኅበረ ቅዱሳን «ስም» የተዘጋጀው የሃያ አምስት ዓመት ስትራቴጅክ ሰነድ አንዱ ነው፡፡

በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስ የዚህን ሰነድ አዘጋጆችና አሠራጮች ማንነት በመመርመር ከያዙት ተግባር እንዲቆጠቡ፣ የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ድርጊቱ እንዳይደገም በማያገባቸው የሚገቡ ወሬ አመላላሾች ቦታ ሊያጡ ይገባቸዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከአንድ እስከ አምስት የተዘረዘሩትን እና ሌሎች ጉዳዮችን በአሁኑ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ቢታዩ ቤተ ክርስቲያንን አንድ ርምጃ ወደፊት ለማስኬዝ አመቺ ሁኔታዎች ይፈጠራል ብለን እናምናለን፡፡ ውሳኔው የአባቶቻችን ቢሆንም የእኛ ድርሻ እንደ አካልነታችን የተሰማንን ማቅረብና በአሳብ መደገፍ በመሆኑ ሓላፊነታችንን ተወጥተናል ብለን እናምናለን፡፡

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ዕድገት የሚጋደሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንም ሆነ ሌሎች መሆን አለባቸው የሚሉትን አሳብ ለአባቶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከታች እስከ ላይ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ለተከፈሉ ምእመናንና ለቤተ መቅደስ አገልጋዮች ካህናት ጥንካሬ የቤተ ክርስቲያን ጤናማ አስተዳደር ወሳኝ ነው፡፡ ጠንካራ ዐለት በመዶሻ እንዲሰነጠቅ ጠንካራ ውሳኔ ለቤተ ክርስቲያ ሐዋርያዊ ተልእኮ ወሳኝ በመሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንደ ዐለት ለጠጠረው የቤተክርስቲያኒቱ ሁሉ አቀፍ ችግር የሚሰነጥቅ መዶሻ ነው እንላለን፡፡

በመጨረሻም እግዚአብሔር በአባቶቻችን አድሮ መልካም የሆነውን ሁሉ እንፈጽም ዘንድ በጸሎት ልንበረታ ያስፈልጋል፡፡ ✞

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
ሚዲያ ዋና ክፍል በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በየዐሥራ አምስት ቀኑ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ

አሳታሚ- ማኅበረ ቅዱሳን - ☏ 011–1553555/011–1553442 ✉ 80078 አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል simeatsidk@gmail.com

የሐመርና ስምዐ ጽድቅ ሥርጭት ክፍል
☏ 011– 1234529/30
E-mail: Mk_ distribution@Yahoo.com
ፋክስ (Fax) 0111223393

ሐመር መጽሔትንና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን በጅምላ ማከፋፈል ለምትፈልጉ፤ በስልክ ቁጥር 011 1 24 61 84
በሐመር መጽሔትና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ላይ ምርቶቻችሁን ማስተዋወቅ ለምትፈልጉ በስልክ ቁጥር 011 1 24 61 81

- ዋና አዘጋጅ - አሥራት ከበደ
- አዘጋጅ - ሊቀጠበብት ሐረገወይን አገዘ
- ከፍተኛ ሪፖርተሮች - መ/ር መንግሥተአብ አበጋዝ
  - ደረጀ ትዕዛዙ
- ሪፖርተሮች - ይብረሁ ይጥና
  - ዲ/ን ኅሩይ ባየ
- የኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወ/ጻድቅ
- ረ/ኮምፒዩተር ዲዛይን - ልደት አስፋው
- ኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ጸዳሉ ሁንዴሳ
  - ደብረወርቅ ተክለጽዮን

«ማኅበረ ቅዱሳን»፡- እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል፡፡

«ስምዐ ጽድቅ»፡– የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ«የእውነት ምስክር» ማለት ነው፡፡

፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፲፯/ ቅጽ ፲፰ ቁጥር ፪፻፷፭ ከግንቦት ፲፮ - ፴ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሐድሶ. . .

ከገጽ ፪ የዞረ::

ቀላል እንዳልሆነ ተረዱ፡፡ ስለዚህ አዲስ ስልት መቀየስ አስፈለጋቸው፡፡ ይህም "እናድሳለን" በሚል ሽፋን ከውጭ ወደ ውስጥ ሠርጎ በመግባት ምእመኑን እስከ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ የመረከብ ስልት ነው፡፡ ይህንም ኬንያ ውስጥ የሚታተመው "The Horn of Africa, Challenge and Opportunity" የተባለው መጽሔት "ዓላማው አዲስ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት አይደለም፤ ቤተ ክርስቲያኗን (ኦርቶዶክስን) መለወጥ (ፕሮቴስታንት ማድረግ) እንጂ - The objective is not to set up a new church as such but to introduce reforms within the church" በማለት ገልጾ ነበር፡፡ (The Horn of Africa, Challenge and opportunity, p. 6)

ስለዚህ አዲሱ ስልት *"የጥንቷ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትክክል ነበረች - The ancient Orthodox was the right Church"* የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያንን ከውጭ ከመቃወም ይልቅ ውስጥ ገብቶ ምእመን፣ ካህን፣ መነኩሴ፣ ሰባኪ … መስሎ ከፕሮቴስታንት እምነትና ባህል ውጭ ያለውን ነገር ሁሉ *"ይህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም፣ ይህን እገሌ የጨመረው ወይም የቀነሰው ነው … '* እያሉ ቤተ ክርስቲያኗ ኦርቶዶክሳዊ ዶግማዋ፣ ቀኖናዋና ትውፊቷ በሙሉ ጠፍቶ ሙሉ በሙሉ ፕሮቴስታንት እስክትሆን ድረስ መሥራት ነው፡፡

ይህን ስልታቸውንም በኅትመቶቻቸው በይፋ ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌም በአንድ ስልታቸውን ይፋ ባደረጉበት መጽሔታቸው ላይ እንዲህ ብለዋል፡-

"ታዲያ እርሷን (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን) የማዳኑ ሥራ ከየት ይጀምር? እዳር ሆኖ አንዳንድ ምርኮኛን ማፍለሱ የሚፈለገውን የኦተቤን ተሐድሶ ሊያመጣ ይችላልን? አገልግሎቱ ከየት ወደ የት ቢሄድ ይሻላል? ማለት ከውስጥ ወደ ውጭ ወይስ ከውጭ ወደ ውስጥ? በውስጧ እያሉ የወንጌል እውነት ለተገለጠላቸው አገልጋዮቿ እንደ ውጊያ ቀጠና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ምሽግ በአሁኑ ጊዜ የማስለቀቅና የጠላትን ወረዳ ከጥቃት ነጻ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ያለው በሁለት ወገን ነው፤ … "

ይልና ቀጥሎም ወደ ግባቸው ለመድረስ መደረግ አለበት ያሉትን እንዲህ ዘርዝረዋል፡-

***ውስጥ ያሉት እግዚአብሔር በሰጣቸው የውጊያ ቀጣና ውስጥ ሆነው በታማኝነት በእግዚአብሔር ቃል ምስክርነትና በጸሎት ውጊያውን መቀጠል አለባቸው፡፡***

***በውስጥ ላለው ለዚሁ ውጊያ*** በወንጌል የታደሱ ክርስቲያኖች ሁሉ እንደ ሙሴ እጃቸውን ወደ ላይ በማንሣት ታላቁን ርዳታ ማድረግና በደጀንነት መቆም ይገባቸዋል፡፡

እነዚህ በወንጌል ተሐደሶ አግኝተናል የሚሉ ሁሉ በውጭ ሆነው ወደ ውስጥ የሚያደርጉትን ውጊያ መቀጠላቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ***ለውስጠኛው ውጊያ የሚያገለግል ትጥቅ ያላቸውን ወደ ውስጥ ማስገባትና የውስጠኛውን የውጊያ መስመር ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል፡፡***

*" … በዚህ የተቀናጀ ስልት <u>መንፈሳዊው ጦርነት ቢቀጥል</u> በውስጥ የተሰለፈው ሠራዊት (በተሐድሶ ስም የሚሠራው የፕሮቴስታንት ክንፍ) እያጠቃ ወደ ውጪ ሲገሰግስ፣ በውጭ ያለውም (በግልጽ ፕሮቴስታንት ሆኖ የሚሠራው) ከበባውን አጠናክሮ ወደ ውስጥ ሲገፋ እግዚአብሔር በወሰነው ቀን የውስጡና የውጪው ሠራዊት ሲገናኙ በውስጧ የመሸገው ጠላት መሸነፉን በሚመለከት በአንድነት የድል ዝማሬ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡"* (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002 ዓ.ም)

***ይህ ሁሉ የሚያሳየው***

ሀ) በቤተ ክርስቲያኒቷ ላይ በይፋ የተቀናጀ ጦርነት ያወጁባት መሆኑን፣

ለ) የጦርነቱ አንዱ ስልት ውስጥ ሆኖ በውስጥ አርበኝነት መሥራትና መዋጋት መሆኑን፣

ሐ) የጦርነቱ ዓላማ ጠላት የተባለችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማፍረስ መሆን ነው፡፡

## የተሐድሶው ዘመቻ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

ተሐድሶዎች ያሰቡትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እንዳለች ፕሮቴስታንታዊ አድርጎ ለውጦ ለመረከብ ያላቸውን ምኞትና ዓላማ እውን ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሁለቱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### *ሀ) የሐሰት ውንጀላዎችን መፍጠርና ማሰራጨት*

ሌባ ሲሰርቅ የሚያየውን ወይም መስረቁን ያወቀበትን ሰው ይወዳል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው፡፡ እንደዚሁም እነዚህ በውጫቸው የቤተ ክርስቲያንን ለምድ የለበሱ፣ በውስጣቸው ግን ኦርቶዶክሳዊ የሆነውን እምነትና ባህል አጥፍቶ የምዕራባውያን ባህል ተሸካሚ ለማድረግ የሚሠሩ ክፉ ሠራተኞች (ፊል.፫÷፪) ዓላማቸውንና ስልታቸውን የሚያውቅባቸውን ማንኛውንም ግለሰብም ሆነ ማኅበር አምርረው ይጠሉታል፣ ይፈሩታልም፡፡፡

በእነ ማርቲን ሉተር በአውሮፓ ተካሒዶ ምዕራባውያንን ወደ እምነት አልባነትና ክህደት ማድረሱን ዛሬ በተግባር ያስመሰከረውን ተሐድሶ (ፕሮቴስታንት) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ላይ እውን በማድረግ ይሁዳ ስለ ሠላሳ ብሩ ሲል ጌታውንና አምላኩን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመሸጥ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጋር "አሳልፌ እንድሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ?" (ማቴ.፳፮÷፲፭) ብሎ ጌታውን ለሽያጭ እንዳቀረበ፣ እነዚህም ስንቅና ተስፋ የሚሰጧቸውንና ስልት ነድፈው ከርቀት እያሳዩ የሚያሠሯቸውን የላኪዎቻቸውንና የጌቶቻቸውን ምኞት ለማሳካት ዕንቅፋት ይሆኑብናል የሚሏቸውን ሁሉ ማኅሩን አምርረው ወተቱን አጥቁረው በማሳየት ስማቸውን በማጥፋት እንዲጠሉ ለማድረግ ይሞክራሉ፡፡

ከዚህ ተግባራቸው ለምሳሌ ያህል ብነጠቅስ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በተሰጠው ሕገ ደምብ መሠረት በአባቶች ቡራኬና ፈቃድ የተመሠረተውንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ሆኖ ዓቅሙ በፈቀደ መጠን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘውንና ይህን ለቤተ ክርስቲያናችን እጅግ አደገኛ የሆነ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ምንነት በማጋለጥ ለሕዝብ የሚያስረዳውን ማኅበረ ቅዱሳንን ስሙን በኅትመቶቻቸውና በልዩ ልዩ መንገድ ማጥፋትና ሰይጣናዊ አስመስሎ መሳል አንዱ ስልታቸው ነው፡፡ ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

*"ማቅ (ማኅበረ ቅዱሳን) ያለ እኔ ቤተ ክርስቲያን፣ ሀገርና መንግሥት የለም ብሎ በጭፍን የሚያስብ ስለ ሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሌላ መንፈሳዊ ማኅበርም ሆነ ጉባኤ ለማየት ዓይኑ የተሸፈነ ነው፡፡ ራሱን የቅዳሴ፣ የቅኔና የመጻሕፍት ማስመስከሪያ ቤት መምህራን አድርጎ በማየቱ በእርሱ እጅ ፈቃድ ያላገኙ ሰባኪያንና መዘምራን ቢፈጠሩ የተለመደው የኮሚኒስቶች ፍልስፍና (የሀሰት ስም የማጥፋት ቅስቀሳውን) ያወርድባቸዋል፡፡"* (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2002፣ ገጽ 1፣ ርእሰ አንቀጽ)

እንግዲህ ይህን የሚለው አካል በግልጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ተሐድሶ ያስፈልጋታል እያለ በዚሁ ጋዜጣ የገለጸው የተሐድሶ ድርጅት ነው፡፡ ልዩነቱ የዓላማ መሆኑን ራሳቸው ተናግረው ሲያበቁ እንደ ገና መልሰው ተሐድሶ መባልን የሐሰት ስም ማጥፋት ዘመቻ ነው ይላሉ፡፡ አንባቢዎቻቸው ይህን እንኳን ማገናዘብ አይችሉም ብለው ይሆን?

*"የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት እግዚአብሔር ፍጹም ጨካኝ ስለ ሆነ ስለማይሰማንና በርኅራሄ ከእርሱ የተሻሉ ቅዱሳን በፊቱ ቆመው እንዲለምኑልን የእነርሱ ልመና ግድ ብሎት ስለሚምረን በአማላጅነት እንመን ይላል፡፡"* (ይነጋል፣ 1997 ዓ.ም. ገጽ 123)

"ማኅበረ ቅዱሳን የተባለው ይህ የሰይጣን ማኅበር አሁን ወደ ነፍሰ ገዳይነት ሊገባ ራሱን እያዘጋጀ ነው፡፡" (ይነጋል፣ 1997 ዓ.ም. ገጽ 127)

ይህ የስም ማጥፋት ዘመቻ በሀገር ውስጥ ባሉ ሚዲያዎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ዋናው የተሐድሶ ዘመቻ አርቃቂዎችና ስልት ነዳፊዎች በሆኑት በምዕራባውያን ፓስተሮችም በብዛትና በዓይነት የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም ዊሊያም ብላክ የተባለው አሜሪካዊ ፓስተር አናሲሞስ በተባለው የጦማር መድረኩ ላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ማፈራረስ እንደሚቻልና በአሁኑ ወቅትም የእርሱና መሰል ድርጅቶች ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እየተዋጓት እንደሆነ "Struggle for the soul of the Ethiopian Orthodox Church" በተሰኘው ጽሑፉ ላይ በሰፊው ገልጧል፡፡ የፕሮቴስታንት ጉዳይ አስፈጻሚ የሆነው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ምን ማለት መሆኑን ለዓላማቸው መሳካት እንቅፋት ሆኖብናል ያለውን ነገር ሲናገር ገልጾታል፤ እንዲህ ሲል፡-

"Working against both the ongoing creep of Western values and the attempts by Reformists to restore the church, a reactionary movement called Mahebere Kidusan and led by members of the hierarchy and priests and others, are seeking to fend off any changes and to preserve aspects of the Church which they feel are crucial to their identity and Ethiopia's place in the world. … በሀገሪቱ ውስጥ እየተንሰራፋና ሥር እየሰደደ ያለውን ምዕራባዊ ባህልና በተሐድሶ አራማጆች ቤተ ክርስቲያኒቷን ለማደስ የሚደረገውን ጥረት ሁለቱንም የሚቃወምና ለዚህም እየሠራ ያለ አድኃሪ የሆነ ማኅበረ ቅዱሳን የሚባል እንቅስቃሴ አለ፡፡ ይህ ማኅበርም ቤተ

> ይልቁንም አሁን ሃይማኖታቸው በግልጽ ፕሮቴስታንት (ተሐድሶ) የሆኑና ብዙ ጉድ ያለባቸው፣ የምግ ባር ድቀት ያንገላታቸው፣ የሃይማኖት አባት ሆነው ምእመናንን ለማስተ ማርና ለመምራት ቀርቶ ተነሳሒ ለመሆን እንኳ የከበዳቸው ሰዎች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ጵጵስና ለመሾም የሲኖዶስ ስብሰባ በመጣ ቁጥር አፋፍ ላይ እየደረሱ እየተ መለሱ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲሁ ከቀጠለ እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን የጳጳሳትን አስኬማ ደፍተው፣ በትረ ሙሴ ጨብጠው፣ "አቡነ" እገሌ ተብለው ላለመምጣታቸው ምን ዋስትና አለ? "ሞኝ ቢቃጡት የመቱት አይመስለውም" እንደሚ ባለው እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎችን ለጵጵስና ዕጩ አድርጎ እስከ ማቅረብ ደረጃስ እንዴት ሊደረስ ቻለ?

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል::

# ቅዱስ ሲኖዶስ

ከቤተክርስቲያን መመሥረት በፊት በነበረው ዘመን በተለይ በዘመነ ብሉይ የቤተክርስቲያን ሲኖዶስ የመሰለ ወይም ከሲኖዶስ ጋር በጥቂቱም ቢሆን የሚመሳሰሉ ጉባኤዎች /ስብሰባዎች/ ተደርገው እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን::

እግዚአብሔርም ለሙሴ «በሕዝቡ ፊት እለፍ ከእስራኤልም ሽማግሌዎችን ከአንተ ጋር ውሰድ፤ ባሕሩንም የመታህበትን በትር ይዘህ ሒድ እነሆም እኔ በዚያ በኮሬብ በዐለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ፤ አንተም ዐለቱን ትመታለህ፤ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከዚያ ውኃ ይወጣል» አለው::

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር በኮሬብ በነበረው ዐለት ያደረገው ስብሰባ በሐዲስ ዘመን ከተሰበሰቡት ሲኖዶሶች /ጉባኤዎች/ ጋር ይመሳሰላል::

ሙሴ በሌላ ጊዜ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከእስራኤል ሽማግሌዎችና ከካህናቱ ጋር ወደ ደብረ ሲና ለመውጣት ያደረገው ስብሰባ ከሲኖዶስ ጋር የሚመሳሰል ነው፤ /ዘፀ.፲፱፥፩-፳፭/:: በተለይም የእግዚአብሔርን ክብር ያዩ ዘንድ ሙሴና የእስራኤል ሽማግሌዎች፣ ከካህናቱ ጋር ወደ ደብረ ሲና ወጥተው በሩቅ ቆመው ለእግዚአብሔር ክብር ስግደት በማቅረብ የተሰበሰቡት ስብሰባ ሲኖዶስን የሚመስል ነው እንላለን:: /ዘፀ.፳፬፥፩-፲፩/::

በሌላ በኩል የእስራኤል ልጆች ወደ ምድረ ከነዓን ለመግባት በሲና ምድረ በዳ በሚጓዝበት ወቅት የሚበላ ዳቦና የሚጠጣ ውኃ ሲያጡ ወደ ሙሴ ይጮኹ ነበር:: ሙሴም የሕዝቡን ችግር ለእግዚአብሔር እያሰማ ሕዝቡ ማግኘት የፈለጉትን ያስጣቸው ነበር:: በዚሁ መሠረት አንድ ቀን የእስራኤል ልጆች እጅግ ጎምጅተው «የምንበላው ሥጋ ማን ይሰጠናል? በግብፅ ሳለን ያለዋጋ ዓሣውንም፣ ዱባውንም፣ በጢሁንም፣ ነጭ ሽንኩርቱንም፣ ቀይ ሽንኩርቱንም እንደ ልብ እንበላ ነበር:: አሁን ግን ሰውነታችን ደረቀች፣ ዐይናችንም ከዚህ መና በቀር የሚያየው የለም» ብለው አጉረመረሙ::

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ ከሕዝቡ ሰባ ሽማግሌዎችን የሕዝቡ አለቆችና ሽማግሌዎች ይሆኑ ዘንድ መርጦ ወደ መገናኛው ድንኳን እንዲያቀርባቸው አዘዘው::

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሰባዎቹን ሰዎች ከሕዝቡ መርጦ ወደ ማደሪያው ድንኳን አቀረባቸው:: እግዚአብሔርም ለሙሴ ከሰጠው መንፈስ ወስዶ በእነርሱ አሳደረባቸው:: መንፈስም /መንፈስ ቅዱስም/ በሰባው ሰዎች ላይ ባደረ ጊዜ ትንቢት ተናገሩ:: በዚያው ወቅትም ከሰባው ጋር ተመርጠው ወደ ድንኳኑ ሳይመጡ በሕዝቡ ሰፈር የቀሩ ኤልዳድና ሞዳድ የተባሉ ሰዎች ነበሩ:: መንፈስም ባሉበት ወረደባቸው:: እነርሱም ትንቢትን ተናገሩ:: ከዚያ በኋላ ከእነዚህ ሰባ ሁለት ሽማግሌዎች ጋር ሙሴ የሕዝቡን ችግር እንዲሸከም ታዘዘ::

ከዚያም እግዚአብሔር ከእነዚህ ሰባ ሁለት ሽማግሌዎች /፸፪ ሊቃናት/ ፊት በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ልጆች ሥጋ አዘነበላቸው፤ /ዘኁል.፲፩ ፥፩-፲፫/::

በመሆኑም የእነዚያ ሰባ ሁለት ሽማግሌዎችና የሙሴ በማደሪያው ድንኳን መሰብሰብና የመንፈስ ስጦታን

ከገጽ ፩ የዞረ::

መቀበል በዘመነ ሐዲስ ከተደረጉት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤዎች ጋር የሚመሳሰል ነው::

ኢያሱም ከሙሴ ዕረፍት በኋላ ሕዝበ እስራኤልን ለመምራት እንዲችል በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሙሴ ኢያሱን በማኅበሩ ሁሉ ፊት /በጉባኤ ፊት/ በአንብሮተ እድ እንደሾመው መጽሐፍ ይነግረናል፤ /ዘኁል.፳፯፥፲፭-፳፫/:: ስለሆነም የኢያሱ በጉባኤው ፊት መሾም ሰባቱን ዲያቆናት በአንብሮተ እድ ከሾሙት ከሐዋርያት ጉባኤ ጋር የሚመሳሰል ነው፤ /ሐዋ.፮፥፩-፯/::

እንደዚሁም በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በምዕራፍ ፪፥፲፪ እና በምዕራፍ ፬፥፴ ላይ እንደተገለጸው፤ ደቂቀ ነቢያት በነቢዩ በኤልሳዕ ፊት ያደረጉት ስብሰባ ከቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ጋር የሚመሳሰል ነው::

ስለዚህ በዘመነ ሐዲስ ቅዱሳን ሐዋርያት ካደረጉት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፊት በዘመነ ብሉይ በሕዝበ እስራኤል መካከል የተከሰተውን ችግር ለማስወገድና ሕዝበ እስራኤልንም በጉባኤ ውሳኔ ለመምራት ቅዱስ ሲኖዶስን የመሰሉ ስብሰባዎች መደረጋቸውን በአጭሩ ለማስረዳት ተሞክሮአል::

## ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት

የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳን የክርስቶስን ቤተክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ መምራት የጀመሩት ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው:: ቅዱሳን ሐዋርያት ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን በሥምረት ለመምራት በዘመናቸው የተለያዩ ጉባኤዎችን እንዳደረጉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ይኸውም በአስቆሮታዊው ይሁዳ ምትክ ሌላ ሐዋርያ ለመምረጥ ያደረጉት ስብሰባ ነው::

ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ቅዱስ ሉቃስ እንደመሰከረው ለደቀመዛሙርቱ አርባ ቀን እየተገለጸላቸው፣ ስለእግዚአብሔር መንግሥትም እየነገራቸው /እያስተማራቸው/ በብዙም ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖና ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ለእነርሱ እየታያቸው ቆየ /ሐዋ.፩፥፩-፬/:: ስለ እርሱ የተጻፉትንም መጻሕፍት ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው:: እንዲህም አላቸው፣ «ክርስቶስ መከራ ይቀበላል፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ይነሣል፣ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል» ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል:: እናንተም ስለዚህ ምስክሮቹ ናችሁ:: እነሆም «አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፣ እናንተ ግን ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ብሎ አዘዛቸው:: ከዚያም ወደ ቢታንያ ወደ ደብረ ዘይት አወጣቸው፣ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው፣ ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ፣ ወደ ሰማይም ዐረገ» /ሉቃ.፳፬፥፵፬-፶፫/:: እነርሱም ጌታ ወዳረገበት ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች /ሁለት መላእክት/ በአጠገባቸው ቆሙ:: ደግሞም እንዲህ አሉአቸው «እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ ትኩር ብላችሁ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችሁ? እነሆ ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁ

**ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከአርድእትና ከምእመናኑ ጋር ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ፤ ሐዋርያት በወሰኑት ውሳኔ ሕዝቡ በሙሉ ተደስተው ሰባቱን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች መርጠው ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አቅርበው የሾሙት ጉባኤ በመሆኑም ጉባኤው ከወሰነው ታላቅ ቁም ነገር የተነሣ «ሲኖዶስ» ተብሎ ሊጠራ ይችላል::**

እንዲሁ ይመጣል» ሲሉ ነገሩአቸው:: /ሐዋ.፩፥፮-፲፩/::

ሐዋርያትም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ከደብረ ዘይት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ:: ከዚያም ዘወትር እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያወደሱ /እየባረኩ/ በመቅደስ /በጽርሐ ጽዮን/ ኖሩ /ሉቃ.፳፬፥፶/:: በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ በአጠቃላይ መቶ ሃያ ሰዎች ያህል ባሉበት ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ በይሁዳ ቦታ ሌላ ሰው መተካት እንዳለበት ንግግር አደረገ::

«ወንድሞች ሆይ፣ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለሆናቸው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው ይፈጸም ዘንድ የተገባ ሆነ፤ እርሱም ከእኛ ጋር ተቆጥሮ ነበርና፣ ለዚህም ሐዋርያዊ አገልግሎት ታድሎ ነበርና» ብሎ በመናገር ስለ አስቆሮቱ ሰው ስለ ይሁዳ ዐመፅና አሟሟት ገለጻ አደረገ::

ከዚያም ይሁዳን ስለሚተካው ሰው አስመልክቶ «ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ እኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፣ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል» ብሎ ገለጸ::

ወዲያውም በጉባኤው ስምምነት መሠረት የመቶ ሃያው ማኀበር አባላት ከነበሩት መካከል በርያስ የተባለውን ዮሴፍንና ማትያስን፣ሁለቱን በመካከል አቆሙአቸው:: ስለ እነርሱም ሲጸልዩ፤ «የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፣ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ይሔድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና
ሐዋርያነት ቦታን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው» ብለው ጸለዩ:: ቀጥሎም ዕጣ ተጣጣሉላቸው፤ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀ /ወጣ/:: እርሱም ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ» /ሐዋ. ፩፥፲፭-፳፮/::

ማትያስን መርጠው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲሾመው ከጸለዩ በኋላ ቁጥሩ ከሰብዐ ሁለቱ አርድእት ውስጥ የነበረው ረድእ ማትያስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተሹሞ ከቀሩት ሐዋርያት ጋር ገብቶ ተቆጠረ:: በዚህ ሁኔታ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው ከአርያም /ከሰማይ/ የሚላክላቸውን ኃይል ማለት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ደጅ እየጠኑና እየተጠባበቁ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሰነበቱ::

በዓለ ሃምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ጌታ ባረገ በዐሥረኛው ቀን ሁሉም በአንድነት አብረው እየጸለዩ ሳለ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ወደ እነርሱ ድምፅ መጣ:: ተቀምጠው የነበሩበትንም ሁሉ ሞላው፤ እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች /የእሳት ላንቃ/ የመሰሉ ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጠባቸው፣ መንፈስ ቅዱስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በልዩ ልዩ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር፤ /ሐዋ.፪፥፩-፭/::

በዚህ ጊዜ ጌታችን ከትንሣኤው በፊት «እኔ በአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ /ጰራቅሊጦስ/ ከአብ የሚወጣ /ዘይሠርጽ/ የጽድቅ /የእውነት/ መንፈስ በመጣ ጊዜ ስለ እኔ ይመሰክራል፣ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ጀምሮ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» ብሎ የተናገረው ተስፋ ተፈጸመ::

ደግሞም ወደ ሰማይ በሚያርግበት ወቅት «እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፣ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሲል የሰጠው ሰማያዊ ተስፋ ተፈጸመ፤ /ሉቃ.፳፬፥፵፱፤ ሐዋ.፪፥፵፫/::

ከዚህ በላይ እንዳየነው ከበዓለ ሃምሳ ዋዜማ ጀምሮ በኢየሩሳሌም በጽርሐ ጽዮን የተካሔደው የመጀመሪያው የሐዋርያትና የሰብዓ አርድእት ጉባኤ እጅግ በጣም ታላቅ ጉባኤ ስለነበረ የመጀመሪያው የሐዋርያት ሲኖዶስ ሊባል ይገባዋል:: ምክንያቱም:-

፩. ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም የነበረችበት ጉባኤ በመሆኑ፤
፪. ቅዱስ ማትያስን የመረጠና የሾመ ጉባኤ በመሆኑ፤
፫. ለሐዋርያትና ከእነሱ ጋር በጸሎት ተሰብስበው ለነበሩት ሁሉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ጉባኤ በመሆኑ፤
፬. በዚያው ቀን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በመውረዱ ምክንያት በሐዋርያት ስብከት ሦስት ሺሕ የሚያህል ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የቤተክርስቲያን አባል የሆነበት ቀን በመሆኑ ጉባኤው የቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ሲኖዶስ ተብሎ ሊጠራ ይገባል::

በመሆኑም በቤተክርስቲያን ታሪክ የቅዱስ ሲኖዶስ ታሪካዊ አመሠራረት ከዚህ ቀዳሚው ጉባኤ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: በሌላ መንገድም በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደተመዘገበው ከሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በየጊዜው በተለያዩ ቦታና ዘመን የተደረጉ የአህጉረ ስብከት /Regional or Local/ ሲኖዶሶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉ ሲኖዶሶች መሠረታቸው የኢየሩሳሌሙ የመጀመሪያው የሐዋርያት ጉባኤ ነው ቢባል እርግጥ ነው::

## ሁለተኛው የሐዋርያት ሲኖዶስ

ሁለተኛው የሐዋርያት ሲኖዶስ ተብሎ ሊጠራ የሚገባው ጉባኤ፤ ራሳቸው ሐዋርያት ተሰብስበው የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን በአንብሮተ እድ የሾሙት ዐቢይ ሲኖዶስ ተደርጎ እንደነበረ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል::

ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት /ደቀመዛሙርት/ ምእመናንን በሙሉ ጠርተው፤ «እኛ የእግዚአብሔርን ቃል /ወንጌልን/ ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም:: ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን፣ መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፣ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፣ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን» ብለው ገለጹላቸው::

ይህም ቃል /ንግግር/ ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው:: ስለዚህም እምነትና መንፈስ ቅዱስም የመላበትን ሰው እስጢፋኖስን፣ ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም፣ ኒቃሮናንም፣ ጢሞናንም፣

ወደ ገጽ ፺ ዞሯል::

# ቅዱስ ሲኖዶስ

ጸርሜናንም መረጡ፡፡ በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው ሐዋርያት ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው /ሐዋ. ፮÷፩-፯/፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከአርድእትና ከምእመናኑ ጋር ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ፤ ሐዋርያት በወሰኑት ውሳኔ ሕዝቡ በሙሉ ተደስተው ሰባቱን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች መርጠው ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አቅርበው የሾሙት ጉባኤ በመሆኑም ጉባኤው ከወሰነው ታላቅ ቁም ነገር የተነሣ «ሲኖዶስ» ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

ነገር ግን እንደሚታወቀው በቤተ ክርቲያን ታሪክ መሠረት በተለምዶ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጉባኤ ወይም የመጀመሪያው ሲኖዶስ ተብሎ የሚጠራው በኢየሩሳሌም በ፶/፶፩ ዓ.ም የተደረገው ጉባኤ ነው፡፡

## ሦስተኛው የሐዋርያት ሲኖዶስ

ይህ በኢየሩሳሌም የተደረገው ሦስተኛው የሐዋርያት ጉባኤ ቅዱስ ሲኖዶስ ተብሎ ሊጠራ ይገባል፡፡ ነገር ግን በተለምዶ የመጀመሪያው የሐዋርያት ጉባኤ /ሲኖዶስ/ እየተባለ መጠራቱ ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡

ጉባኤው ሊደረግ የተፈለገበት ዋና ምክንያት የሚከተለው ነው፡፡ በሐዋርያት ዘመን በአንጾኪያ ከተማ በነበረችው ቤተክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፡፡ እነርሱም በርናባስ፣ ኔጌር የተባለው ስምዖን፣ የቀሬናው ተወላጅ ሉክዮስ፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የነበረው የሄሮድስ ባለሟል ምናሔና ሳውል እነዚህ ሁሉ ጌታን እያመለኩና እየጾሙ ሳለ መንፈስ ቅዱስ፤ «በርናባስንና ሳውልን ለጠ ራኋቸው ሥራ ለዩልኝ፤ ፍልጥዎሙ ሊተ ለበርናባስ ወለሳውል ለገብር ዘፈቀድክዎሙ» አላቸው፡፡ እነርሱም መንፈስ ቅዱስ እንደነገራቸው አደረጉ፡፡ ከጾሙ ከጸለዩና እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው /ሐዋ.፲፫÷፩-፫/፡፡

ከዚያም ጳውሎስ በርናባስና ማርቆስ ከሌሎቹ ጋር ወደ ቦታው ሁሉ እየዞሩ ወንጌልን ሰበኩ፡፡ በየሰንበቱም በአይሁድ ምኩራብ እየተገኙ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ስለ ትንሣኤው ይሰብኩ ነበር፡፡ እንደዚሁም በልስጥራ፣ በደርቤን፣ በጲስድያ፣ በጵንፍልያ፣ በጴርጋሞን፣ በጵርሄንም የእግዚአብሔርን ቃል /ወንጌልን/ እየሰበኩ ሕዝቡን ያጽናኑ ነበር፡፡ በአንጾኪያም በደረሱ ጊዜ ቤተክርስ ቲያንን /ምእመናንን/ ሰብስበው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ ለአሕዛብም የሃይማኖት ደጅ እንደተከፈተላቸው ተናገሩ፡፡

ነገር ግን በዚያን ጊዜ አንዳንዶች ከይሁዳ ሀገር ወደ አንጾኪያና ወደ ሌሎቹ አውራጃዎች ወረዱና «እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» እያሉ ወንድሞችን /ምእመናንን/ ያስተምሩ ጀመር፡፡ በዚያን ጊዜ በእነዚያ ሰዎች በጳውሎስና በበርናባስ መካከል ብዙ ጠብና ክርክር ተፈጠረ፡፡ ጠቡና ክርክሩ እያየለ በሔደ ጊዜ ጳውሎስ፣ በርናበስና ከእርሱ ጋር የነበሩ የወንጌል አገልጋዮች ተነጋግረው ወደ ሐዋርያት ለመሔድ ወሰኑ፡፡ ወደ ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ ቤተክርስቲያን /ምእመናን/ ሐዋርያትና ቀሳውስት /Apostles and the Elders/ ተቀበሉአቸው፡፡

እነ ጳውሎስም በዞሩባቸው አህጉረ ስብከት ሁሉ ያደረጉትን /የፈጸሙትን/

ከገጽ ፭ የዞረ፡፡

የወንጌል አገልግሎትና የገጠማቸውን ችግር ሁሉ በዝርዝር ሪፖርት አቀረቡ፡፡ በዚያን ጊዜ በጌታ ካመኑት ከፈሪ ሳውያን ወገን የሆኑት ሰዎች ተነሥ ተው «ትገርዙአቸው ዘንድና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዝዙአቸው ዘንድ ይገባል» ብለው ለሐዋርያት ተናገሩ፡፡ እነሆም በዚያን ጊዜ ሐዋርያትና ቀሳውስት / Apostles and the Elders/ ለመመካከርና ለመወሰን በአንድነት ተሰበሰቡ፡፡ የዚህ ዐቢይ ሲኖዶስ ሰብሳቢ /ሊቀመንበርም/ ቅዱስ ያዕቆብ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም እንደነበር በቤተክርስቲያን ታሪክ ተገልጿል፡፡

በጉባኤውም በቀረበው ጉዳይ ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያውን ንግግር አደረገ፡፡

ከቅዱስ ጴጥሮስ ንግግር በኋላም ጳውሎስና በርናባስ ተነሥተው እግዚአ ብሔር በእጃቸው በአሕዛብ መካከል ያደረገውን ምልክትና ድንቅ ነገር ሁሉ ለሲኖዶሱ ተረኩ፡፡ ከዚያም የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው የኢየ ሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስና የጉባኤው ሰብሳቢ ቅዱስ ያዕቆብ ንግግር አደረገ፡፡

ከቅዱስ ያዕቆብ ንግግር በኋላ ሐዋርያትና ቀሳውስት / Apostles and the Elders/ ከቤተክርስቲያኑ /ምእመናኑ/ ሁሉ ጋር ከእነርሱ የተመረጡትን ሰዎች ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ይልኩ ዘንድ ተስማሙ፡፡ ከእነ ጳውሎስ ጋር እንዲሔዱ የተመረ ጡትም በርስያን የተባለው ይሁዳና ሲላስ ነበሩ፡፡ የጉባኤውም አባላት በጉባኤ የተወሰነውን ውሳኔ ጽፈው በተመረጡት ወንድሞች እጅ ላኩ፡፡

መልእክተኞቹም ተሰናብተው ወረዱ፤ ሕዝቡንም ሰብስበው ከሐዋ ርያት ጉባኤ የተላከውን ደብዳቤ ሰጡአ ቸው፡፡ ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሣ ደስ አላቸው፡፡ ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነቢያት ነበሩና ወንድሞችን በብዙ ቃል መክረው አጽናኑአቸው፡፡ አያሌ ቀንም ከእርሱ ጋር ከተቀመጡ በኋላ ከወንድሞቻቸው በሰላም ተሰና ብተው ወደ ሐዋርያት ተመለሱ፡፡

ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊትና ሲኖዶሳዊት ለመሆንዋ ተደጋግሞ የተነገረ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ቅዱሳን ሐዋርያት ቤተክርስቲያንን በስብከተ ወንጌል ስለአሰባሰቡና ስለአጠናከሩ ቤተክርስቲያን በሲኖዶስ እየተመራች ከዚህ ዘመን በመድ ረስዋ ሲኖዶሳዊት /ጉባኤያዊት/ እየተባለች ትጠራለች፡፡

ከቅዱሳን ሐዋርያት ቀጥለው የተነሡት አባቶችም ቤተክርስቲያንን በሚመሩበት ወቅት፡-

ሀ. የቤተክርስቲያንን ቅዱሳት መጻሕፍት ከመናፍቃን መጻሕፍት ለመለየትና ቁጥራቸውን በቀኖና /በሕግ/ ለመወሰን፤

ለ. ሥርዐተ ቅዳሴንና ሥርዐተ ጸሎትን በቀኖና /በሕግ/ ለመመደብ፤

ሐ. አጽዋማትንና በዓላትንም ለመወሰን የሲኖዶስ ስብሰባ በማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ ወስነዋል፡፡

በሌላ በኩልም ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በየጊዜው መናፍቃን /ሐራ ጥቃዎች/ በተነሡ ጊዜ ቅዱሳን የቤተክርስቲያን አባቶች ርትዕት፣ ስብሕት /ኦርቶዶክስ/ ሃይማኖትን ለመጠበቅ ሐራጥቃዎችን በቀኖናዋ ውግዘት ለማስወገድ በሲኖዶስ እየተሰ በሰቡ ይወስኑ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በየሀገሩ የአካባቢ ሲኖዶሶች /Regional or Local Synods/ ተደር ገዋል፡፡

ከተደረጉት ሲኖዶሶችም ለአብነት ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

*፩. በ፪፻፶፯ ዓ.ም በካርቴጅ የተደ ረገው ሲኖዶስ፡-* በዚህ የአካባቢ /Regional/ ሲኖዶስ ሰማንያ አራት ኤጲስ ቆጶሳት ተሳትፈዋል፡፡ የሲኖዶሱ ሰብሳቢ ቅዱስ ሲፕሪያኖስ ነበር፡፡ በዚህ ጉባኤ ሥርዓተ ጥምቀትንና መናፍቃንን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የኤጲስ ቆጶሳትን ሥልጣን የተመለከቱ ቀኖናዎች ተወስነዋል፡፡

፪. ፪፻፷፬-፪፻፷፱ ዓ.ም በተከታታይ በአንጾኪያ ሲኖዶስ ተደርጎአል፡፡ በዚህ ሲኖዶስ ዐሥራ አራት ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው በምስጢረ ሥጋዌ የጎድረትንና የፅምረትን /ምንታዌ አካላትን/ ትምህርት ማስፋፋት የሞከ ረውን ኤጲስ ቆጶስ ጳውሎስ ሳምሳጢን መክረው አልመለስ ስላለ አውግዘው ከቤተክርስቲያን ለይተውታል፡፡

፫. በዚሁ ዓይነት በአንካራ በ፫፻፲፬ ዓ.ም ፣በጋንግራ ፫፻፵፫ ዓ.ም፣ በሳርዲካ በ፫፻፵፫ ዓ.ም፣ በአንጾኪያ በድጋሚ በ፫፻፵፩ ዓ.ም፤ በላኦዶቂያ በ፫፻፷፬ እና በ፫፻፹፩ ዓ.ም የተጠራው ሲኖዶስ ስድሣ ቀኖናዎችን ዐውጆ አል፡፡ እንደዚሁም በድጋሚ በካርቴጅ በ፬፻፲፱ ዓ.ም የተሰበሰበው ሲኖ ዶስ ፻፴፫ ቀኖናዎችን ዐውጆአል፡፡ ይህ ሲኖዶስ «የአፍሪካ ኤጲስ ቆጶሳት ሲኖዶስ» በሚል መጠሪያ ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሐዋርያውያነ አበው /Apost olic Fatheres/ የቤተክርስቲያንን አስተዳደርና የቤተክርስቲያንን ችግር በሲኖዶስ እየተሰበሰቡ በመመርመርና አስፈላጊውንም በመወሰን ቤተክር ስቲያንን መርተዋል፡፡ ያውም ከሰባ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፫፻፲፫ ዓ.ም ድረስ የነበረው ጊዜ አሕዛብ በቁጥር የበዙ በትና በመንግሥት አስተዳደርም አጠቃላይ ሥልጣን ግን የጨበጡበት ዘመን ስለነበረ፤ በዚህ ዘመን ከፀረ እግዚአብሔርና ከፀረ ክርስትና ኃይሎች ጋር በመጋደል በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ስለ ህልዎተ እግዚአ ብሔርና ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖታቸው መሥዋዕት ሆነው የተሰውበት ዘመን ነበር፡፡ በመሆኑም ዘመኑ ዘመነ ሰማዕታት እየተባለ ይጠራል፡፡

> **ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊትና ሲኖዶሳዊት ለመሆንዋ ተደጋግሞ የተነገረ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ቅዱሳን ሐዋርያት ቤተክርስቲያንን በስብከተ ወንጌል ስለአሰባሰቡና ስለአጠናከሩ ቤተክርስቲያን በሲኖዶስ እየተመራች ከዚህ ዘመን በመድ ረስዋ ሲኖዶሳዊት /ጉባኤያዊት/ እየተባለች ት ጠራለች፡፡**

> **ከቤተክርስቲያን መመሥረት በፊት በነበረው ዘመን በተለይ በዘመነ ብሉይ የቤተክርስቲያን ሲኖዶስ የመሰለ ወይም ከሲኖዶስ ጋር በጥቂቱም ቢሆን የሚመሳሰሉ ጉባኤዎች /ስብሰባዎች/ ተደርገው እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን፡፡**

## ዓለም አቀፍ ሲኖዶሶች

ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞ ከረው በአካባቢ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ወይም ውስጥ የቀኖና ወይም የዶግማ ችግሮች ሲከሰቱ በአቅራቢያ ሀገሮች ከሚገኙ ኤጲስ ቆጳሳት ሲኖዶሶች እየተጠሩ ለተነሡት ችግሮች መፍትሔ ይሰጡ ነበር፡፡ ነገር ግን በአካባቢ በሚደረጉት ሲኖዶ ሶች የማይፈቱ ከሆኑ በዚያኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ ከሚባለው የዓለም ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የጋራ የሆነ ዐቢይ ዓለም አቀፍ ጉባኤ / Ecumenical Council/ እያደረጉ ችግሮቹን በመመ ርመር መፍትሔ ይሰጡ ነበር፡፡

የመጀመሪያው የኒቂያ ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ በ፫፻፳፭ ዓ.ም ኒቂያ በተባለች ከተማ ከመደረጉ በፊት አርዮስና ኑፋቄአዊ ትምህርቱን መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት አርዮስ በኖረበትና በተነሣበት ሀገር በእስክንድርያ በመጀመሪያ በ፫፻፳ ዓ.ም፤ ቀጥሎም በ፫፻፳፩ ዓ.ም ሲኖዶስ ተደረገ፡፡ የዚያ ሲኖዶስ ሰብሳቢ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው እለ እስክንድሮስ ዘእስክንድርያ ነበር፡፡ ችግሩ በዚያ ዓይነት ይፈታል ተብሎ ቢሞከርም ሰባት መቶ ደናግል፣ ዐሥራ ሁለት ዲያቆናት፣ ስድስት ቀሳውስት /የደብር አለቆች/ ከሦስት የሚበልጡ ኤጲስ ቆጶሳት ትምህርቱን ተቀብለው አርዮስን ስለደገፉ አርዮስ በሲኖዶሱ ምክር ሊመለስ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ከአራት ዓመት በኋላ በሊቀ ኤጲስ ቆጶሳት እለእስክንድሮስ አስተባባሪነት በንጉሠ ነገሥቱ በቆስጠንጢኖስ ተባባሪነት ፫፻፲፰ አበው ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳት በኒቂያ ከተማ በ፫፻፳፭ ዓ.ም የሲኖዶስ ስብሰባ አድርገው ከኑፋቄው አልመለስ ያለውን እልከኛውን አርዮስንና ትምህ ርቱን አውግዘው ሃይማኖትን አጸኑ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በአንድ ልብ ሆነው «አንቀጸ ሃይማኖት /ጸሎተ ሃይማኖት/» የተባለውን የዶክ ትሪን ዐዋጅ አጸደቁ፡፡ ከሃያም ያላነሱ ቀኖናዎችን አጽድቀው አሠራጩ፡፡

ከዚያም በመቀጠል ከሃምሳ ስድስት ዓመት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን የካዱ መናፍቃን /ሐራጥቃዎች/ /heretics/ ተነሥተው በምሥራቅ በኩል የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ባስቸገሩ ጊዜ በቁስጥንጥንያ ከተማ በ፫፻፹፩ ዓ.ም ከመላው ዓለም አንድ መቶ ሃምሳ አበው ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰበሰቡ፡፡ «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያነሰ ነው /ሕጹጽ ነው/» ብለው የተነሡትን መቅዶን ዮስንና ተከታዮቹን ተመክረውና ተለምነው ከክሕደታቸው ስላልተ መለሱ አወገዙአቸው፡፡ ትምህርታ ቸውንም በማውገዝ ውሳኔ አሳለፉ፡፡ በመቀጠልም ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመርኮዝ «መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አምላክ መሆኑን፣ ጌታና ማኅየዊ እየተባለም ከአብና ከወልድ ጋር አንድ ባሕርይ ስለሆነ ከሁለቱ አካላት ጋር በአንድ መለኮት እንደ ሚመሰገንና እንደሚሰ ገድለት፤ እንዲሁም ከአብ ብቻ መሠረጹን ገልጸው ወሰኑ» ውሳኔውም ከኒቂያው አንቀጸ ሃይማኖት/ከጸሎተ ሃይማኖት/ ጋር ተጨምሮ እንዲጻፍ አደረጉ፡፡ በዚሁም መሠረት በአሁኑ ዘመን በመላው ዓለም በየቤተክር ስቲያኑ በተለያየ ቋንቋ የሚጸለየው ጸሎተ ሃይማኖት «የኒቂያ- ቁስጥ ንጥንያ አንቀጸ ሃይማኖት»/ Nicene-Constantinople Creed/ እየተባለ ይጠራል፡፡

ከቁስጥንጥንያው ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ በኋላ ሃምሳ ዓመታት ቆይቶ ንስጥሮስ የተባለ መናፍቅ ተነሣ፡፡ እሱም የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ነበር፡፡ ከ፬፻፳፯ዓ.ም ጀምሮ በቁስጥንጥንያ ምስጢረ ሥጋዌን በማፋለስ «ክርስቶስ ሁለት አካላት፣ ሁለት ገጻት፣ ሁለት በመስተጻምር /በሲናፊያ/ አንድ የሆኑ ባሕርያት ያሉት ነው» እያለ አስተማረ፡፡ በዚህም መርሐ መሠረት «ቃለ እግዚአ ብሔር /ሎጎስ/ እና ክርስቶስ በመስተ ፃመር /በሲናፊያ/ አንድ ስለሆኑ ክርስቶስ አንድ ነው» ብሎ አስተማረ፡፡

ከዚሁም አያይዞ «ድንግል ማርያም እግዚአብሔርን ልትወልድ አትችልም፤ ከእርስዋ የተወለደው ክርስቶስ ነው፡፡ ስለሆነም እርስዋን ወላዲተ ክርስቶስ እንጂ ወላዲተ እግዚአብሔር /ወላዲተ አምላክ/ አንላትም» በማለት አስተማረ፡፡ በዚሁ ችግር ምክንያት በ፬፻፴፩ ዓ.ም ከመላው ዓለም አበው ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በኤፌሶን ተሰብስበው ሦስተኛውን ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ አደረጉ፡፡

ንስጥሮስን ሦስት ጊዜ ጠርተውት አልቀርብም ስላለ የጻፉቸውን መልእ

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል፡፡

# ቅዱስ ሲኖዶስ

ከገጽ ፮ የዞረ::

ክታት ተመልክተውና ስሙን ጠርተው አወገዙት:: ክርስቶስንም «ወልድ ዋሕድ፣ ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው፣ ከሁለት ባሕርይ / ከመለኮትና ከትስ ብእት/ አንድ ባሕርይ፣ አንድ አካል» መሆኑን የሚያረጋግጡትን የቅዱስ ቄርሎስን መልእክታት ተቀብለው አጸደቁ:: ቅድስት ድንግል ማርያምንም «በአማን ወላዲተ አምላክ» መሆንዋን አረጋገጡ::

በሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ እየተመራ ወደ ኤፌሶን የመጣው የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶሳት ቡድን ግን የንስጥሮስን ውግዘት ተቃወመ:: በዚህ ምክንያት የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን በኤፌሶን ከተሰበሰቡት የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተለየች:: እስከ ፬፻፴፫ ዓ.ም በእስክ ንድርያና በአንጾኪያ አብያተ ክርስ ቲያናት መካከል መለያየት ጠነከረ፤ የጠብ ግድግዳም ተመሠረተ:: በ፬፻፴፫ ዓ.ም ግን በንጉሠ ነገሥት ቴኦዶስዮስ ካልዕ አስታራቂነት ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ታረቁ:: በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንደርያና በዮሐንስ ዘአንጾኪያ መካከልም ሰላም ተመሠረተ:: በዚሁ ዕርቅ መሠረት አንጾኪያውያን አበው በኤፌሶን የተወሰነውን ውሳኔ ተቀበሉ:: በንስጥሮስ መወገዝና መወገድም ተስማሙ:: አንድነትም ተመሠረተ::

ቅዱስ ቄርሎስ በ፬፻፵፬ ዓ.ም ሲያርፍ በኋላ የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ የነበረው ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ፬፻፵፰ዓ.ም ከቁስጥ ንጥንያ በሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ፍላብያን የሚመራ የአካባቢው ኤጲስ ቆጶሳት የተሳተፉበት ሲኖዶስ /Local Synods/ ተደረገ:: ወደዚህም ሲኖዶስ አውጣኪ ተከሶ ቀረበና ተወገዘ:: እርሱም ወደ ሮምና ወደ እስክንድርያ ፓትርያክ «አላግባብ ተወገዝሁ» ብሎ አቤቱታ ጻፈ::

«የአውጣኪን ጉዳይ ለመመርመ ርና ተረፈ ንስጥሮሳውያንን ለማስወገድ» በሚል አጀንዳ ለሁለተኛ ጊዜ በ፬፻፵፱ ዓ.ም በኤፌሶን ሲኖዶስ ተደረገ:: በስብሰባውም አንድ መቶ ሠላሳ አምስት ኤጲስ ቆጶሳት ተሰበሰቡ:: የሲኖዶሱ ሊቀ መንበር ፓትርያክ ዲዮስቆሮስ ሆነ:: በአጀንዳው መሠረት ጉዳዮች ተመረመሩ:: አውጣኪንም መረመሩት::

ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ፍላብያኖንስና ፌኦዶሪትን ግን ጉባኤው መርምሮ መንፈቀ ንስጥሮሳውያን ሆነው ስላገኛቸው በጊዜያዊ ውግዘት ተቀጥ ተውና ታስረው እንዲቆዩ ተደረገ:: የፖፕ ልዮን ጦማረ ሃይማኖትም ቀርቦ በዲዮስቆሮስና በሌሎች የጉባኤው አባላት ተመርምሮ ከንስጥሮስ ትምህርት ጋር ተዛምዶ ስለተገኘ በጦማሩና በጦማሩ ባለቤት ላይ ውግዘት አከል ተግሳጽ እንዲተላለፍባቸው ተደረገ::

ፖፕ ልዮን ግን ይህንን ታሪክ ሰምቶ በዲዮስቆሮስ ጥርሱን ነከሰ:: ጉባኤውንም «የወረበሎች ጉባኤ» /Synods of Listriks/ ብሎ ጠራው:: ከዚህ ንዴት የተነሣ በሁለተኛው ዓመት በ፬፻፶፩ ዓ.ም በኬልቄዶን ጉባኤ እንዲደረግ ተወሰነ:: በዚህ ጉባኤ ስድስት መቶ ሠላሳ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው በልዮን መልእክተኞች እየተመሩ ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ከንጉሡ ጋር ተሻርከው ከመንበሩ አወረዱት::

ታስሮም በደሴተ ጋግሪ ሦስት ዓመት ተቀመጠ:: ከዚያም እንዳለ በእስራትና በበሽታ ምክንያት ፬፻፶፬ ዓ.ም ዐረፈ::

ከቅዱሳን ሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ያየነው ታሪክ እንደሚያስረዳን ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተክርስቲያን መሪ እንደሆነ ነው:: ቤተክርስቲያንም ከተጠቀሰው የመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ መለኮታዊ አገልግሎትዋን ስታካሒድ የኖረችው በመንፈስ ቅዱስ በሚመራው በቅዱስ ሲኖዶስ በመመራት ነው::

በቤተክርስቲያናችን ትውፊት መሠረትም የሐዋርያትንና የአር ድእት ቀኖናዎች የሊቃውንትም ጭምር ሲኖዶስ /መጽሐፈ ሲኖዶስ/ እየተባለ ይጠራል:: ከዚህ በላይ እንደተ መለከትነውና እንደምናውቀው በአካባቢ የተነሡትን የሃይማኖትም ሆኑ የቀኖና ችግሮች በመጀመሪያ በአካባቢው ሀገሮች ባሉት ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳት ሲኖዶስ ወሳኝነት ይፈቱ ነበር:: ከእነርሱም አቅም በላይ ሆነው የተገኙ ችግሮች ደግሞ «ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ» /Ecumenical Synods/ እየተጠራ ሲወሰን እንደነበረ ተመልክተናል::

ከዚያም ሌላ በየትኛውም ሀገር የምትገኘው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን /Local Synods/ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ አንድ ማእከል አንድ ሲኖዶስ ብቻ እንዳላት ተገንዝ በናል:: ለምሳሌ የኢየሩሳሌም ቤተክርስ ቲያን በአንድ የኢየሩሳሌም ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን በአንድ የእስክንድርያ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የቁስጥንጥንያ ቤተክርስቲያን በአንድ የቁስጥንጥንያ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የግሪክ ቤተክርስቲያን በአንድ የግሪክ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ሲመሩ መኖራቸውን እናውቃለን::

ለአንዲት ነጻ ሀገር አንድ ፓርላሜንት /One Parliament/ ብቻ እንዳላት ሁሉ ለአንዲት ነጻ ቤተክርስቲያንም አንድ ቅዱስ ሲኖዶስ /Autocephalous Church/ ብቻ እንዳላት የታወቀና የተረጋገጠ ነው::

ቅዱስ ሲኖዶስ ስንል /በተለይ ሀገራዊ Local/ የሚከተሉትን ነገሮች ይይዛል:-

- ኤጲስ ቆጶሳት
- የታወቀ ሕጋዊ መንበር
- ታሪካዊና ሕጋዊ መሠረት

ለምሳሌ የግብፅን ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ብንመለከት

- ወደ ሃምሳ የሚጠጉ ኤጲስ ቆጶሳት
- የእስክንድርያ /የቅዱስ ማርቆስ/ መንበር
- በታሪክ የታወቀና ቅዱስ ሲኖዶሱ ያጸደቀው ሕግ አላቸው

የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ:-

● ኤጲስ ቆጶሳት

● የአዲስ አበባ መንበር /መንበረ ፓትርያክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም የሚገኝ/

በቤተክርስቲያን ሕግ የጸደቀ ከመነሻውም /ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ሲጀመር የነበረ ሕግ አላት::

✞

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ . . .

ከገጽ ፬ የዞረ::

ክርስቲያንን ለመለወጥ የሚደረ ገውን ማንኛውንም ነገር ለመከላከልና ለራሳቸው ማንነትና ኢትዮጵያ በዓለም ስላላት ቦታ አስፈላጊ ነው የሚሉትን የቤተ ክርስቲያኒቷን ገጽታ ለመጠበቅ ይፈልጋሉ::"

http://www. compassdirect.org/english/country.ethiopia/11092/

ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚወዱትንና ለእምነታቸውና ለሥርዓታቸው ተቆርቋሪ የሆኑትን ምእመናን፣ ካህናት፣ መነኮሳት ... ሁሉ ማኅበረ ቅዱሳን የሚባል ነገር መኖሩን ከነ ጭራሹ ያልሰሙ ሰዎች ቢሆኑም እንኳ "ማኅበረ ቅዱሳን (ማቅ)" ናቸው የሚል ታርጋ በመለጠፍ ለማሸማቀቅ ይሞክራሉ:: በዚህም የተሐድሶ ጉዳይ የሌለና የሆኑ ቡድኖች ጠብና ሽኩቻ ብቻ ተደርጎ እንዲታይ ይጥራሉ:: እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ለማመን የሚከብዱ የበሬ ወለደ ዓይነት የስም ማጥፋት ወሬዎችን በማኅበሩ ላይ በማሰራጨት ላይ ናቸው:: ለምሳሌም በቅርቡ "የማኅበረ ቅዱሳን የሃያ አምስት ዓመት ስትራቴጂ ነው" በሚል ስም አንድን ሕፃን እንኳ ሊያሳምን በማይችል መልኩ ራሳቸው የፈጠሩትን አሉባልታ የማኅበሩ አስመስለው በሐሰት ማኅተም አትመው በኢንተርኔት አሰራጭተዋል:: እንዲህ ዓይነት የፈጠራ ክሶችንና ስም ማጥፋቶችን ደህና አድርገው ተያይዘዋቸዋል::

*ለ) የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደርና መዋቅር መቆጣጠር*

ተሐድሶዎች ቤተ ክርስቲያኒቷን ለመለወጥና ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ የተመቸች ለማድረግ ይረዳቸው ዘንድ ለመቆጣጠር የሚመኙት አንዱ ነገር የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደርና መዋቅር መያዝ ነው:: ይህን ማድረግ ከቻሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ አንደበት በመናገር፣ ቤተ ክርስቲያን ያልሆነችውን ናት፣ የሆነችውን ደግሞ አይደለችም በማለት ያሰቡትን የተሐድሶ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳቸዋል::

ወደዚህ ግብ ለመድረስም በተለያዩ ጊዜያትና ስልቶች ከመሪጌቶች፣ ከቀሳውስት፣ ከመነኮሳት፣ ከዲያቆናትና ከሌሎችም መካከል በተለያየ ጥቅማ ጥቅምና ድለላ የማረኳቸውንና ያሰለጠኗቸውን ሰዎች በአስተዳደር መዋቅሩ ውስጥ ለማስገባትና ቦታውን ለመያዝ ደፋ ቀና በማለት ላይ ናቸው:: በዚህም የተወሰነ ርቀት መጓዝ ችለዋል:: ይህም በስልታቸው እንደ ገለጹት *"መንፈሳዊ ቀውስ የደረሰበትን አስተዳደር ማረምና ማስተካከል"* (ኖኅተ ብርሃን፣ መጋቢት 2000፣ ገጽ 16) በሚል ሽፋን የሚካሔድ ነው::

ይህን ጉዳይ እስከ የት ድረስ መግፋትና ማድረስ እንደሚፈልጉ ሲገልጹም እንዲህ ብለዋል:-

"ማቅ (ማኅበረ ቅዱሳን) ወደደም ጠላም ቤተ ክርስቲያኒቱ በእውነት በሚወዱትና የወንጌልን እውነት በሚያገለግሉ መምህራንና ሊቃውንት ይህንም እውነት ተቀብለው አምላካቸውን በንጹሕ ልብ ሆነው በሚያመልኩ፣ በተለይም መጪው ዘመን በትካሻቸው ላይ የወደቀባቸው ከመንፈሳዊ ኮሌጆቻችን እየተመረቁ የሚወጡ የወንጌል አርበኞችና ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቁ ዘንድ እግዚአብሔር ጳጳሳት አድርጎ የሾማቸው አባቶች በሚወስዱት የማያዳግም እርምጃ ቤተ ክርስቲያናችን ተሐድሶን ታደርጋለች::" (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2000፣ ገጽ 2)

ጳጳሳት ሳይቀሩ የማያዳግም እርምጃ መውሰዳቸውና ቤተ ክርስቲያኒቱን ማደሳቸው የማይቀር መሆኑን በግልጽ ተናግረዋል:: ስለሆነም ይህን ሕልማቸውን እውን ለማድረግ የቤተ ክርስቲያኗን የአስተዳደር መዋቅር፣ እስከ ጵጵስና ደረጃ ያለውንም መቆጣጠር ዋና ስልታቸው ነው:: ዛሬ የመነኮሱበት የማይታወቅ ሰዎች የአባቶቻችንን ቆብ አጥልቀው መስቀሉን ጨብጠው ቀሚሱን አጥልቀው ካባውን ደርበው፣ ያልሆኑትን መስለው፣ ሌሎችም የነበሩ፣ ዛሬ ግን ያልሆኑ፣ ዓላማቸውን እንደ ይሁዳ ለውጠው የክፋቱ ተባባሪ ሆነው ያሉ ሁሉ በቤተ ክርስቲያኗ ስም ሲጫወቱ ዝም እየተባሉ ስለ ሆነ እነዚህ ሰዎች የነገዩቱ ጳጳሳት የማይሆኑበት ዕድል አይኖርም ብሎ ማሰብ አይቻልም::

ይልቁንም አሁን ሃይማኖታቸው በግልጽ ፕሮቴስታንት (ተሐድሶ) የሆኑና ብዙ ጉድ ያለባቸው፣ የምግባር ድቀት ያንገላታቸው፣ የሃይማኖት አባት ሆነው ምእመናንን ለማስተማርና ለመምራት ቀርቶ ተነሳሒ ለመሆን እንኳ የከበዳቸው ሰዎች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ጵጵስና ለመሾም የሲኖዶስ ስብሰባ በመጣ ቁጥር አፋፍ ላይ እየደረሱ እየተመለሱ ነው:: ይህ ሁኔታ እንዲሁ ከቀጠለ እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን የጳጳሳትን አስኬማ ደፍተው፣ በትረ ሙሴ ጨብጠው፣ "አቡነ" እገሌ ተብለው ላለመምጣታቸው ምን ዋስትና አለ? "ሞኝ ቢቃጡት የመቱት አይመስለውም" እንደሚባለው እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎችን ለጵጵስና ዕጩ አድርጎ እስከ ማቅረብ ደረጃስ እንዴት ሊደረስ ቻለ? ማንነታቸው ተጣርቶ በንስሐ የሚመለሱት ቀኖና ሊሰጣቸው፣ የማይመለሱት ደግሞ ሊለዩ (ሊወገዙ) ሲገባቸው የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ሆነው በቤተ ክርስቲኒያቱ ህልውና ላይ ወሳኝ አካላት ሊሆኑ መታሰቡ በራሱ የሚያሳየው ከባድ ነገር አለ:: እነዚህን ሰዎች በአድባራትና በገዳማት ዕልቅናና በተለያየ ሓላፊነት ከመሾም ጀምሮ ግልጽ የሆነ የአደባባይ ጉዳቸውን ዝም ከማለትና አልፎ አልፎም ከማበረታታት ጀምሮ በቤተ ክርስ ቲኒያቱ አስተዳደር ውስጥ እንዳሻቸው እንዲናኙበት የሚፈቅድና የሚመች የተሐድሶ ሰንሰለት አለ ማለት ይሆን?

እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችና አባቶች እንደ እንጀራ ልጆች እየተቆጠሩና እየተገፉ እነዚህ ተሐድሶዎች ደግሞ ባለሚሎች መስለው ከዚያም አልፎ ለጵጵስና ታጭተው ማየትና መስማት በእጅጉ ያማል፣ ልብንም ያደማል:: ስለዚህ እነዚህ ሰዎች አናት ላይ ወጥተው የጵጵስና መዓርግ ጨብጠው ከመጡ በኋላ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ሊያመጡ ያሰቡትን ስልታዊ አደጋ መገመት ውኃን የመጠጣት ያህል ቀላል ነው:: ስለሆነም እነርሱ ያሰቡት ከባድ ትርምስ ሳይመጣ ‹ሳይቃጠል በቅጠል› እንዲሉ በጊዜ ከጸሎት ጀምሮ ማንኛውም ሊደረግ የሚገባውን የመከላከል ሥራ ከወዲሁ መፈጸም ይገባል:: ቁጭ ብሎ የሰቀሉትን ቆሞ ማውረድ ያቅታልና:: ይህም "እነ እገሌ ምን እየሠሩ ነው?" በሚለው ያልጠቀመን ፌሊጥ ሳይሆን "እኔ ምን አደረግሁ? አሁንስ ምን ማድረግ አለብኝ?" በሚል ሊሆን ይገባል::

**የቤተ ክርስቲያን አምላክ እግዚአብሔር በቤቱ የተሰገሰጉ ይሁዳዎችን የሚያጋልጥበትንና ከመንጋው የሚለይበትን ዘመን ያቅርብልን፣ አሜን::**

✞


**የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የሚል**

**አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ!**





# ማ ኅ በ ረ ቅ ዱ ሳ ን

## የማኅበረ ቅዱሳን ርእይ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል ተጠናክሮ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል በመላው ዓለም ተስፋፍቶ በሃማኖት ጽኑዓን የሆኑ ምእመናን በዝተው ማየት::

## የማኅበረ ቅዱሳን ተልዕኮ

ማኅበረ ቅዱሳን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን የተለያዩ ትምህርተ ሃይማኖት ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ግቢ ጉባኤያትና ምእመናን የወንጌልን ትምህርት፣ ሥርዐትና ትውፊት እንዲያውቁና እንዲጠብቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲጠናከርና አቅሙ እንዲያድግ ማድረግና በየዘመኑ የሚከሰቱ ተለዋዋጭ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመቃኘት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ አገልግሎት ማጠናከር::

## የማኅበረ ቅዱሳን ሕጋዊ የቤተ ክርስቲያን አካልነቱ

ማኅበረ ቅዱሳን ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ባካሔደው የምሥረታ በዓል ላይ የሰንበት ት/ቤቶች ማዳራጃ መምርያ ተገኝቶ ማኅበረ ቅዱሳን በሰንበት ት/ቤቶች ማዳራጃ መምሪያ ሥር መዋቀሩና አገልግሎቱን በይፋ መጀመሩ ገለጠ። ማኅበሩ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ባካሔደው ጠቅላላ ጉባኤ ባጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ አገልግሎቱን ቀጥሏል። በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የማኅበሩ አስፈላጊነትና አገልግሎት መስፋቱን



የካህናት ሥልጠና በሐዋሳ፣በሆሳዕና እና በአፋር ሀገረ ስብከቶች ተሰጥቷል።

በመገንዘብ በቋሚ ሲኖዶስ ደንቡ ጸድቆ አገልግሎቱን በስፋት አጠናክሮ እንዲቀጥል ተደረገ።

በመጨረሻም በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ማኅበሩ ላለፉት አስር ዓመታት የቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዐት ጠብቆ በርካታ የቤተክርስቲያን ልጆች ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያናቸው መጥተው ባላቸው ዕውቀት በቅንነት እያገለገሉ መሆናቸውና ወደፊትም ማኅበሩ ለቤተክርስቲያን የሚኖረውን ጠቀሜታ የተገነዘቡ ቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት በግንቦት ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ባካሔዱት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ መተዳደሪያ ደንቡን በማጽደቅ አገልግሎቱን በስፋትና በምልአት እንዲቀጥል ተወሰነ።

ከላይ እንዳየነው የማኅበሩ ሕጋዊ የቤተክርስቲያን አካልነቱ የሚመነጨው ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የበላይ አካል የሆነው ቅዱስ ስኖዶስ ከሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ነው።

## የማኅበረ ቅዱሳን አመራር አካላት አሰያየም

ማኅበረ ቅዱሳን የተለያዩ የአመራር አካላት አሉት። የማኅበሩ የበላይ አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰይማቸው የሥራ አመራርና የሥራ አሥፈጻሚ ጉባኤያት አባላት፣ ማኅበሩ ባሉት ማዕከላት፣ ወረዳ ማዕከላትና ግቢ ጉባኤያት /ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት/ ጠቅላላ ጉባኤያት የሚሰይሟቸው የሥራ አሥፈጻሚ ጉባኤያት አባላት የማኅበሩ አመራሮች ናቸው።

እነዚህ አመራር አካላት የሚሰየሙበት ሥርዐት መመሪያ ተዘጋጅቶ የሚከናወን ሲሆን በመመሪያው መሠረት በጠቅላላ ጉባኤያት የሚሰየሙ አስመራጭ አካላት በሚያቀርቧቸው እጩዎች የጉባኤያቱ አባላት አስተያየት እንዲሰጡበት ይደረጋል። በአስተያየቱ መሠረት ከሚፈለገው የአመራር አባላት ቁጥር በላይ 50% ከፍ እንዲል ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ተፈላጊው የአመራር አባላት ቁጥር ለመምረጥ ጸሎት ተደርጎ በእጣ የሚለዩ ይሆናል።



ስብከተ ወንጌል ካልተስፋፋባቸው አካባቢዎች የመጡ አዳዲስ ሰባክያን ሠልጣኞች

**ማኅበረ ቅዱሳን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን የተለያዩ ትምህርተ ሃይማኖት ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ግቢ ጉባኤያትና ምእመናን የወንጌልን ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት እንዲያውቁና እንዲጠብቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲጠናከርና አቅሙ እንዲያድግ ማድረግና በየዘመኑ የሚከሰቱ ተለዋዋጭ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመቃኘት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ አገልገሎት ማጠናከር::**



እድሳት የተደረገለት የደብረ ቅዱስ ደብረ ጽጌ የአብነት ትምህርት ቤት

## የማኅበሩ መዋቅራዊ አሠራር

የማኅበሩ መዋቅራዊ አደረጃጀት የቤተ ክርስቲያኒቱን አደረጃጀት በተከተለው መንገድ የሚዋቀር ነው። በዚህ መሠረት በጠቅላይ ቤተክህነት የሚገኙ መመሪያዎች ከማኅበሩ ዋና ማዕከል ዋና ክፍሎች፤ ሀገረ ስብከቶች ከማኅበሩ ማዕከላት፤ ወረዳ ቤተክህነቶች ከማኅበሩ ወረዳ ማዕከላት ጋር አገልግሎት ይፈጽማሉ። የዚህ ዋና ዓላማው የቤተክርስቲያኒቱን አደረጃጀት፣ ሕግና ደንብ በተከተለ መንገድ ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ እንዲያስችልና ለአገልግሎቱ መሳካት ስለሚያስፈልግ ነው።

## የማኅበሩ የውሳኔ አሰጣጥ ሒደት

ማኅበረ ቅዱሳን ባሉት መዋቅሮች የሚታዩ አጀንዳዎች በሙሉ ስምምነት የሚወሰኑ ናቸው። የሚኖሩ የአሳብ ልዩነቶች በየደረጃቸው የሚታዩ ሲሆን በመጨረሻም ጸሎት ተደርጎ በእጣ እንዲወሰኑ ይደረጋል። ማኅበሩ በድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን አያሳልፍም።

## የማኅበሩ የገቢ ምንጮቹና የሒሳብ አሠራሩ

የማኅበሩ የገቢ ምንጮች በመተዳደሪያ ደንቡ በተፈቀደለት መሠረት አባላቱ ካላቸው ማንኛውም የገቢ ምንጭ ቢያንስ ከመቶ አንድ እጅ/1%/ ከሚከፍሉት የአባልነት አስተዋጽኦ፣ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች እንዲሁም በገጠር ጠረፋማና አሕዛብ በበዙባቸው አካባቢዎች ለሚከናወነው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ደረጃቸውን ጠብቀው የሚቀረፁ ፕሮጀክቶችን ከሚደግፉ ምእመናን ገቢ ያገኛል።

ማኅበሩ በዚህ መልኩ የሚሰበስበውን ገንዘብ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው አሠራር መሠረት የሂሳብ ሥራውን ያከናውናል። ይህን የሂሳብ አሠራሩን በሕግ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ያደርጋል።

## ማኅበሩ የሚመራበት የአገልግሎት ዕቅድ

ማኅበሩ በተለያዩ ጊዜያት ባዘጋጃቸው ስትራቴጅክ ዕቅድ ይመራል።ይህ ዕቅድ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል። ለሚመለከታቸው የቤተክርስቲያኒቱ አካላት ይቀርባል። ተገቢው አስተያየትና መመሪያ ይሰጥበታል። የዕቅዱ አፈጻጸም ሪፖርትም በተገቢው ጊዜ ይቀርባል።

## የማኅበሩ አቋም

በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ አምስት እንደ ተገለጠው ማኅበሩ በማናቸውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት የለውም።

## ማኅበሩ አሁን የደረሰበት

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ፵፱ ማእከላት፣ ፬፻ ወረዳ ማእከላትና ግንኙነት

# ማኅበረ ቅዱሳን. . .

ከገጽ 8 የዞረ።



ሰባተኛው ሀገር አቀፍ የግቢ ጉባኤያት /ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች/ ሴሚናር

ጣቢያዎች፣ ፫፻ ግቢ ጉባኤያት /ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት/፣ ከ ፲፩ ሺሕ በላይ አባላት፣ ፬፻፷ በላይ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና ከ፩፱ ሺሕ በላይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

## የማኅበሩ አገልግሎት ክትትልና ግምገማ

የማኅበሩ አገልግሎት በአራት አቅጣጫዎች ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል። የመጀመሪያው በየደረጃው ያሉ የቤተክርስቲያን አካላት ማኅበሩ የሚያዘጋጀው ጠቅላላ ጉባኤ እየተገኙ፣ ዓመታዊ ዕቅድና ሪፖርት እየተላከላቸው ተገቢው አስተያየት መመሪያ ይሰጣሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ቅዱስ ሲኖዶስ በሰጠው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየደረጃው የተቋቋመ የማኅበሩ ኦዲትና ኢንስፔክሽን እና የኤዲቶሪያል ቦርድ አማካይነት የማኅበሩ አገልግሎቱን በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ዶግማ ቀኖና ሥርዐት መጓዙን ክትትልና ግምገማ ይደረጋል።

ሦስተኛ ማኅበሩ ያቀረባቸው ፕሮጀክቶች ተቀብለው አስፈላጊውን ድጋፍ ያደረጉ ምእመናን በአስፈላጊው ጊዜ ሪፖርት ይደርሳቸዋል፣ የመስክ ጉብኝት በማድረግ ሥራዎችን ይመለከታሉ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ወቅት በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ተገኝተው ሀሳባቸውን ይገልጣሉ።

አራተኛው የማኅበሩን የሂሳብ አሠራርና ሰነድ በሕግ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ኦዲተሮች እየተመረመረ ይረጋገጣል፡፡ የኦዲተሮች ሪፖርት ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እና ለሚመለከታቸው የቤተክርስቲያኒቱ አካላት ይቀርባል።

## የማኅበሩ ፈተናዎችና ዋና ምንጫቸው

ማኅበረ ቅዱሳን ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ እንደ ቤተክርስቲያን አካልነቱ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ከፈተና የራቀበት ወቅት የለም ። ይርቃልም ብለን አንጠብቅም ። የፈተና ምንጮቹ ግን ግልጽ ናቸው። በተለይ ታሪካዊት ጥንታዊትና ሐዋርያዊት የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ተመሳስለው በመግባት የሌላውን አስተምህሮ በስውር ለማስረጽና የቤተ ክርስቲያኒቱን ዶግማዋን፣ስርዓቷን በአጠቃላይ ኦርቶዶክሳዊ መልኳንና ለዛዋን በሙሉ በመለወጥ ምእመኗን ከእነ ሕንፃዋ ፕሮቴስታንት አድርጎ ለመውረስ ከሚራወጡ *፡ቤተ ክርስቲያን ትታደስ፡* ብለው ከሚጮኹ እኩያን የሚሰነዘረው ፈተና ዋናና የመጀመሪያው ነው።

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የማኅበሩን ስም በማጥፋት አገልግሎቱን ለማደናቀፍ የተለያዩ ሥልቶች በመጠቀም በርካታ የበጀትና የሰው ኃይል መድበው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በእነርሱ አንደበት፡-

*“ማቅ (ማኅበረ ቅዱሳን) ያለ እኔ ቤተ ክርስቲያን፣ ሀገርና መንግሥት የለም ብሎ በጭፍን የሚያስብ ስለ ሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሌላ መንፈሳዊ ማኅበርም ሆነ ጉባኤ ለማየት ዓይኑ የተሸፈነ ነው፡፡ ራሱን የቅዳሴ፣ የቅኔና የመጻሕፍት ማስመስከሪያ ቤተ መምህራን አድርጎ በማየቱ በእርሱ እጅ ፈቃድ ያላገኙ ሰባኪያንና መዘምራን ቢፈጠሩ የተለመደው የኮሚኒስቶች ፍልስፍና (የሐሰት ስም የማጥፋት ቅስቀሳውን) ያወርድባቸዋል፡፡”* (መጥቅዕ፣ ኅዳር 2002፣ ገጽ 1፣ ርእሰ አንቀጽ)

*“የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት እግዚአብሔር ፍጹም ጨካኝ ስለ ሆነ ስለማይሰማንና በርኅራሄ ከእርሱ የተሻሉ ቅዱሳን በፊቱ ቆመው እንዲለምኑልን የእነርሱ ልመና ግድ ብሎት ስለሚምረን በአማላጅነት እንመን ይላል፡፡”* (ይነጋል፣ 1997 ዓ.ም ገጽ 123)

“ማኅበረ ቅዱሳን የተባለው ይህ የሰይጣን ማኅበር አሁን ወደ ነፍሰ ገዳይነት ሊገባ ራሱን እያዘጋጀ ነው፡፡” (ይነጋል፣ 1997 ዓ.ም. ገጽ 127)

“Working against both the ongoing creep of Western values and the attempts by Reformists to restore the church, a reactionary movement called Mahebere Kidusan and led by members of the hierarchy and priests and others, are seeking to fend off any changes and to preserve aspects of the Church which they feel are crucial to their identity and Ethiopia’s place in the world. … በሀገሪቱ ውስጥ እየተንሰራፋና ሥር እየሰደደ ያለውን ምዕራባዊ ባህልና በተሐድሶ አራማጆች ቤተ ክርስቲያኒቷን ለማደስ የሚደረገውን ጥረት ሁለቱንም የሚቃወምና ለዚህም እየሠራ ያለ አድኀሪ የሆነ ማኅበረ ቅዱሳን የሚባል እንቅስቃሴ አለ፡፡ ይህ ማኅበርም ቤተ ክርስቲያንን ለመለወጥ የሚደረገውን ማንኛውንም ነገር ለመከላከልና ለራሳቸው ማንነትና ኢትዮጵያ በዓለም ስላላት ቦታ አስፈላጊ ነው የሚሉትን የቤተ ክርስቲያኒቷን ገጽታ ለመጠበቅ ይፈልጋሉ፡፡” http://www.compas sdirect.org/english/country.ethiopia/11092/









*የተሰበሰቡ ልባሽ ልብሶች ታጥበው ተተኩሰውና ተሰፍተው የየሀገረ ስብከቶች ሊቃነ ጳጳሳትና የሥራ ሓላፊዎች በተገኙበት ለአብነት ትምህርት ቤት መምህራንን ተማሪዎች እንዲሁም መነኮሳት እንዲደርሳቸው ተደርጓል።*

ሁለተኛው በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የመ/ፓ/ጠ/ቤተ ክህነት የሰንበት ት/ቤቶች ማዳራጃ መምሪያ ማኅበሩ በሚያካሒዳቸው ጠቅላላ ጉባኤያት በመገኘት ተገቢውን አስተያየትና መመሪያ መስጠት፣ የሚቀርብለትን ዕቅድና ሪፖርት መገምገም ቢኖርበትም የመምሪያው ሓላፊ ከተመደቡበት ጊዜ አንሥቶ ይህን ለማድረግ አልቻሉም።

በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ማደራጃ መምሪያው ማኅበሩ ለሚያከናውናቸው አገልግሎቶች መሳካት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ሓላፊነቱ ቢሆንም ግለሰባዊ በሆነ አመለካከትና ፍላጎት ከዚህ በተቃራኒ መልኩ አገልግሎቱን ለማደናቀፍ እተደረገ ያለው ጥረት ከፍተኛ ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በአባቶች ጸሎት እንደተመሠረተ እናምናለን። እንታመናለን። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠችንን የአገልግሎት ሓላፊነት በእግዚአብሔር ኃይል ጠንክረን እንቀጥላለን። በአገልግሎታችን ፍጹም ነን ብለን አናምንም። በቅንነት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠናከር የሚሰጠንን አስተያየትና ማረሚያ ተቀብለን እናስተካክላለን። ስለሆነም እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ አባቶችና ምእመናን በጸሎትና ባለው አቅማችን ሁሉ በጋራ በመሥራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል ተጠናክሮ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል በመላው ዓለም ተስፋፍቶ በሃማኖት ጽኑዓን የሆኑ ምእመናን በዝተው ለማየት አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ይርዳን ። ✞

# “በእንተ ጦማረ ሐሰት”

## በሐሰት የተሠራጨውን ሰነድ በተመለከተ ከማኅበረ ቅዱሳን የተሰጠ መግለጫ

እምነትና ሥርዓቷ ጸንቶ የቆየውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕልውናዋን ለማሳጣት እና ሐዋርያዊ ተልእኮዋን ለማደናቀፍ ቀን ከሌሊት የሚተጉ አካላት የጥፋት ሤራቸውን ከመጎንጎን እና የተቻላቸውን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ ብለው አያውቁም፡፡ ቅድስት ቤተክርቲያን ሕግና ደንብ አውጥታ በመዋቅሯ አቅፋ እንዲያገለግል አደራና ሓላፊነት የሰጠችው ማኅበረ ቅዱሳንም የጥቃታቸው አንዱ ዒላማ ነው፡፡

የማኅበሩን ቀና አገልግሎት ለማስቆም ብዙ ጥረዋል፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት የተመሠረተ እንደ መሆኑ የቅድስት ቤተክርቲያንን መመሪያ ጠብቆ በአባቶች ምክርና ጸሎት እየታገዘ አገልገሎቱን ከመፈጸም ወደኋላ አይልም፡፡ እነዚህ የቅድስት ቤተክርስቲያንን ሐዋርያዊ አገልግሎት የሚፈታተኑ አካላት የማኅበረ ቅዱሳንን ስም በማጥፋት እንደደከሙት ሁሉ፤ ሰሞኑን የማኅበሩን ማኅተም በተጭበረበረ ሁኔታ /ፎርጅድ/ በመጠቀም፣ "የማኅበሩ የሃያ አምስት ዓመት ዕቅድ" ነው በማለት የሐሰት ሰነድ አዘጋጅተው በኢንተርኔት ለማሠራጨት እና ለተወሰኑ ብፁዓን አባቶች እንዲደርስ ለማድረግ ሞክረዋል።

ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎቱ ሁሉ ግልጽ ነው፡፡ ባሳለፋቸው ዐሥራ ዘጠኝ የአገልግሎት ዓመታት ዕቅድና አፈጻጸሙ በየደረጃው ለሚገኙ የቤተክርስቲያን አካላት እና አባቶች እንዲሁም ለማኅበሩ ማእከላትና አባላት በየወቅቱ በሪፖርት የሚገለጽ ውይይት የሚደረግበት ሲሆን በዚሁ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆን ነው። ይህ የማኅበሩ አሠራር በተገቢው ሁኔታ ወደፊትም ይቀጥላል። ሰሞኑን የተሠራጨውን የሐሰት ጽሑፍ በተመለከተ የማኅበሩን መግለጫ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ሰሞኑን “ድንግል ማርያም” በተባለ ፌስ ቡክ (face book) “የማኅበረ ቅዱሳን የረዥም ጊዜ ዕቅድ” በሚል የተበተነ የሐሰት ጽሑፍ እንዲወጣ (Post) መደረጉ ታውቋል። ይህ ጽሑፍ በመጨረሻው ላይ የማኅበረ ቅዱሳን የሃያ አምስት ዓመት ዕቅድ እንደሆነ ይገልፃል። ለመሆኑ ይህ “ጦማረ ሐሰት” ምንጩ ከየት ነው? ጽሑፉ እንዳመለከተው በውኑ የማኅበረ ቅዱሳን ዕቅድ ነውን? ይዘቱና ዓላማውስ ምንድን ነው? ማኅበረ ቅዱሳንስ በዚህ ጽሑፍ ላይ ያለው አቋም ምንድን ነው?

### ምንጩ ከየት ነው?

ጽሑፉ በራሱ ሥልጣን እየተጣጣረም ቢሆን ለመናገር የሚሞክረው "የማኅበረ ቅዱሳን ነኝ" እያለ ነው፡፡ ነገር ግን በመናገር እና በመሆን መካከል ያለውን ርቀት እንዳይፈራገጥ ባስገነዘው ጣዕረ ሞት እንደያዘው የሚይዘውን የሚጨብጠውን ያጣ ወረቀት ነው፡፡ ለዚህም ጽሑፉ ሳያውቀው ምንጩን ሲናገር እናገኘዋለን፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ምንጩ ማኅበረ ቅዱሳን ሊሆን ይችላልን? የሚለውን መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ዕቅድ እያቀደ የእግዚአብሔርን አጋዥነት እየለመነ አገልግሎትን ሲያከናውን ቆይቷል። ዕቅድ ማቀድ በማኅበሩ ዘንድ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ በጥቂቱ የሃያ ዓመት ልምድም ያለው ማኅበር ነው፡፡ አባላቱም ከመንፈሳዊው አገልግሎት ባሻገር በየተሠማሩበት የሙያ ዘርፍ ዕቅድ እያቀዱ ራሳቸውን በዘመናዊው አሠራር ያበለጸጉ ከመሆናቸው አንጻር መሠረታዊ የዕቅድ አዘገጃጀት ዕውቀት ያላቸው መሆኑን ልንጠራጠር አንችልም፡፡

የተበተነው ጽሑፍ ያውም ሁለት ከወገብ በታች /ግማሽ ገጽ/ የሆኑ ወረቀቶች ላይ ማኅበሩ የሃያ አምስት ዓመት ዕቅድ ተብሎ ተዘርዝሯል፡፡ እንዲህ ዐይነቱ የሃያ አምስት ዓመት ዕቅድ ማቀድ በአዘጋጆቹ ዘንድ የተለመደ ይሆናል እንጂ በማኅበረ ቅዱሳን ዘንድ የለም። የማኅበሩ የአራት ዓመት ስልታዊ ዕቅድ እንኳን የተዘጋጀው በሃምሳ አምስት ገፆች ነው፡፡

ስልታዊ ዕቅድ እንደመሆኑ መጠን በዘመናዊው አሠራር የራሱ ቅርጽ (format) አለው። ቢያንስ ቢያንስ መግቢያ፣ የማኅበሩን ማንነት፣ የማኅበሩ ዓላማ፣ ርእይ፣ ተልእኮ፣ እሴት፣ የባለድርሻ አካላት ትንተና፣ ውጫዊ አካባቢ ትንታኔ፣ እንዲሁም አስፈላጊነቱ ሌሎች ትንታኔዎች ምቹ እና ፈታኝ ሁኔታዎች፣ የምቹ እና ፈታኝ ሁኔታዎች ምዘና፣ ወሳኝ ጉዳዮች፣ ስልታዊ ዕቅድ ዓላማ፣ ግብና ስልት፣ ዝርዝር የአፈጻጸም መርሐ ግብር እንዲሁም የክትትልና የግምገማ ሥርዐት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

በዚህ ቅርጽ መሠረት የማኅበረ ቅዱሳን ስልታዊ /ስትራቴጂክ/ ዕቅዱን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያን አካላት በማቅ ረብ በዕቅዱ መሠረት አገልግሎቱን በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አሠራሩ ያልተመቻቸው አካላት የጕንዮሽ ዕቅድ በማቀድ የራሳቸውን የፈጠራ ሥራ አቅርበዋል። ማኅበረ ቅዱሳንን ለመወንጀል ታስቦ የሐሰት ሰነድ (forged document) ተዘጋጅቶ የተበተነበትም ምክንያት ያንን ዕቅድ አባቶች እንደ ማያውቁት በማስመሰል ነው፡፡

### የፖለቲካ አጠቃቀም

ማኅበሩ በመዋቅሩ ሥር ያሉትን አካላት በራሱ መጥራት የተሳነው አስመስለው ቀርጸውታል፡፡ ለማሳያ የሚሆነውም በዝርዝር ዕቅዱ ውስጥ በአንድ ላይ "በየንዑሳን ቅርንጫፍ በኩል" የሚል ሐረግ ይገኛል። ሲጀምር ማኅበሩ ቅርንጫፍ የሚባል ምንም ዓይነት መዋቅር የለውም፡፡ ከዋናው ማእከል ቀጥሎ ያሉት ማእከላት ይባላሉ እንጂ ንዑሳን አይባሉም። ይህም አጠቃቀሙ ሌላ አካል መሆኑን ያሳያል፡፡ በአስገራሚ ሁኔታ የተበተነው ወረቀት አንድ ተማሪ ክፍል ውስጥ ገብቶ ሲማር ከሚይዘው ማስታወሻ እንኳ ያነሰ፤ ዕቅድ መባል ካለበት እንኳ የጨነገፈ ዕቅድ ነው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ሊያወጣው አይችልም። በዚህ መስፈርት እንኳን ቢታይ ዕቅዱ በምንም መለኪያ የማኅበረ ቅዱሳን አለመ ሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ራሱን ሲጠራ ”ማህበረ ቅዱሳን” ብሎ አያውቅም፡፡ "ዕቅድ" የሚለውን ቃል ዐቅድ የሚለውን ተክቶ ለጥቅም እንዲውል አድርጎም አያውቅም፡፡ እነዚህን የተጠቀመው ጽሑፍ ራሱን እርቃኑን አቁሞ የማኅበረ ቅዱሳን አለመሆኑን የገለጠበት ዘርፍ ነው፡፡

ወረቀቱ ስለ ዕቅድ የሚናገር ከሆነ የተግባራዊነት ዘመኑ ከመቼ እስከ መቼ እንደሆነ እንኳ አለመገለጹ ድንገቴ እንደ ወራጅ ውኃ የፈሰሰ የጥቂቶች አሳብ እንጂ ዕቅድ አለመሆኑን ያሳብቅበታል፡፡

የስሕተት ሙሻዙር የጠመዘዛቸው አዘጋጆች እንደመሰላቸው እነርሱ ያስቀመጧቸውን በወንጀል ደረጃ የሚፈረጁ አደገኛ አሳቦች በማኅተም አትሞ በቲተር እና በፊርማ አስደግፎ ራሱን ለአደጋ አጋልጦ የሚያስቀምጥ ተቋም በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ይገኛል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው፡፡ በተሠራጨው ዕቅድ ላይ የተቀመጡት አሳቦች አሉታዊ እና አፍራሽ አስተሳሰቦች እንደመሆናቸው መጠን ማኅበሩ የቱንም ያክል ክፉ ነው ተብሎ ቢታሰብ እንኳ እንዲህ ያለ ዕቅድ በዚህ መልክ አዘጋጅቶ እና አንድ ቦታ አጠራቅሞ ይገኛል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ያንን ያክል ክፋት ማርገዝ የቻለ እኩይ ሕሊና ቢኖር እንኳ አካሔዱን እና አቀማመጡን አይጠብብበትም ነበር የሚለው ለአንባቢ የሚተው ውሳኔ ይሆናል፡፡

እነዚህን አካሔዶች ጠቅልለን ስንመለከታቸው ምንጩ ለጊዜው የማኅበረ ቅዱሳንን በመጨረሻም የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ጥፋት ሌት ተቀን ከሚለማመኑ አካላት የተቀዳ ለመሆኑ ከቶውኑ ማን ይመራመራል?

መጽሐፍ “በክፋታቸው እየባሱ ይሔዳሉ” እንዳለው የማኅበረ ቅዱሳን መኖር የእግር እሳት ስለሆነባቸው በምን መንገድ ስሙን ቢያጠፉ ተቀባይነት ሊያገኙ እንደሚችሉ ሁልጊዜ ወጥመድ ያጠምዳሉ፡፡ እስካሁን ድረስ የእግዚአብሔር ቸርነት ከልክሏቸው አልተሳካላቸውም እንጂ የወገባቸው የሐሰት ዝናር ሲያልቅባቸው በማኅበሩ ወንበር ተቀምጠው የሚናገሩ በማስመሰል ማኅበሩ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ተልእኮ እንዳለው አድርገው ሊያቅዱለት ፈለጉ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ካባ ለብሰው ያቀዱለት ዕቅድ ግን ከተለመደው ክሳቸው የወጣ አለመሆኑ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ማኅበሩን ለምን ትቃወማላችሁ ሲባሉ ይሰጡት የነበረውን መልስ ዕቅድ ነው ብለው አቀረቡት እንጂ ምንም አዲስ ነገር አላመጡም፡፡ ስለሆነም በዚህ በጻፉት ዕቅዳቸው ምክንያት ማንም ሊደነግጥላቸው አይችልም፡፡ በተቻላቸው መጠን የመጨረሻዋን ጥይት ለመተኮስ ሲጥሩ መልሶ ራሳቸውን ወጋቸው። በተጉበትም መጠን በመጐዳታቸው አሟሟታቸውን ለማሳመር የሐሰት እና የጥፋት ዕቅድ ለማኅበሩ አወጡለት።

የሚጠባበቁት ውጤት በእነዚያ ወንጀሎች ምክንያት ያቀዱለት አካል ዕለቱኑ ታንቆ ዕለቱኑ ሲሞት ለማየት በጉጉት ኮርቻ ላይ ተቀመጡ፤ የፈለጉት ማኅበሩ ከእነርሱ ጐን ቆሞ ቤተክርስቲያንን እንዲያጠፋ ላቸው ነበር፡፡ ግን ምን ያደርጋል? እነርሱም ታወቁ ሕልማቸውም መከነ፡፡

### ራሱን በራሱ ሲቃረን

አንድ ተቋም ራሱን ሲገልጽ ”እኛ” በሚል ባለቤት ሊናገር እንደሚችል የተረዳ ነገር ነው፡፡ በጽሑፉ ላይ ግን አባቶችን አባላት በማድረግና ”ስብሰባቸው ላይ” የሚል አባባል ተጠቅመዋል፡፡ ስለራሱ ዕቅድ የሚናገር ሰው ”በስብሰባችን ላይ” ይላል እንጂ ”ስብሰባቸው ላይ” እንዴት ሊል ይችላል? በተጨማሪም ”በራሱ ጠቅላላ ጉባኤ መምራት” በማለት ማኅበሩ ራሱን ”እርሱ” እያለ እንዲጠራ አድርገው ጽፈዋል፡፡ እንዲሁም ”ካህናቱን ለድርጅቱ ሠራተኞች አድርጎ መቅጠር” በሚለው ዕቅዳቸው ላይ ”እርሱ” ብሎ ራሱን እንዲጠራ አድርገውታል፡፡

ከእነዚህ አገላለጾች የምንረዳው የሆነ አካል ራሱን አስገድዶ የማኅበሩ አካል አድርጎ በመቁጠር ስለ ማኅበሩ ሆኖ እንዲጽፍ እንደተጨነቀ ያሳያል፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል አልተቻለውም። ራሱን ጠፍሮ በማሠር ስለ ማኅበሩ እንዲናገር አሰቃየው እንጂ ስለ ሌላ ማኅበር እንደሚናገር ተገልጦበታል፡፡ ጸሐፊው ያለ እርሻው የበቀለ ከሌላ ዘር የመጣ ነውና የራሴ ነው ያለውን ማኅበር ”እነርሱ” ”እርሱ” እና ”እኛ” እያለ ጠራው፡፡

ያልሠለጠነ ውሸታም በመሆኑ እንዲጽፍላቸው የቀጠሩትን ሰዎች አጋለጣቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወዴት መሸሸግ ይቻላል? የጨለማው መጋረጃ ተቀደደባቸው፣ ከእነ ተንኮላቸው እጅ ከፍንጅ ተያዙ፡፡ ወዲህና ወዲያ እንዳይሉ በራሳቸው ገመድ ተጠፍንገው ታሠሩ፡፡ እግዚአብሔር ይፍታችሁ ከማለት ውጭ ምን እንላለን?

**ይህንን ጽሑፍ ያሰራጩት አካለት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ማንም ሰው መገመት ይችላል፡፡ ከመገመትም አልፎ አገኘሁ ብሎ ማኅበሩን ለማጥላላት የሚጠቀምበት ሁሉ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ተቀባዮችም የሰጪዎችን ማንነት ያውቃሉ፡፡ እንዲያውም ከማብራሪያ ጋር እንደተቀበሉ ይታመናል ፡፡**




ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል፡፡

# የቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ እና. . .

ከገጽ ፲፪ የዞረ።

እና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀሱት ሦስት ናቸው።

የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርክና ዘመን አጭር መሆን ነው። ከግማሽ ምእተ ዓመት ብዙም ያልዘለለው መንበረ ፓትርክና /በራሳችን አበው ራሳችንን የመምራት ልምዳችን/ ያልዳበረ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ቅዱስ ሲኖዶስ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድትመራባቸው የሚያ ወጣቸው ሕጐችና ደንቦች በየትኛውም ደረጃ ባሉ የሥራ ሓላፊዎችና ተቋማት ላይ በትክክል ተፈጻሚ ሆነው ተፈ ጻሚነታቸውን የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት የአሠራር ሥርዐት አለመዘርጋቱ ሲሆን፤ ሦስተኛው የተጠ ያቂነት አሠራር አለመኖሩ ነው። ይህም ሲባል ሥራዎች ተቆጥረውና ተሠፍረው አይሰጡም። ቢሠጡም ደግሞ የሚፈጸሙትን የአሠራር ጉድለ ቶች ተከታትሎ ርምጃ የመውሰዱ ባሕሉ ጭራሽ የለም ማለት ይቻላል።

እንግዲህ ቅዱስ ሲኖዶስ የመንፈሳዊ እና የአስተደደራዊ ልዕልናው መገለጫ የሆኑ ውሳኔዎቹን ከግብ ከማድረስ አኳያ ሦስት ነገሮች ላይ ቢያተኩር

> *እንግዲህ ይህን ሁሉ ላደረግልዎ ለልዑል እግዚአብሔር ምን ዋጋ ይከፍሉት ይሆን? ኢትዮጵያ ካለፈው ይልቅ ለሚመጣው ተስፋ ታደርግዎታለች። ይህን አይታው የማታውቀውን ማዕረገ ተክህኖ ለማስገኘት ዕድልዎ ምክንያት ሆኖ እንዳስገኘላት እንደዚሁም በአባትነትዎ ጸሎትና በመንፈሳዊ መሪነትዎ መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶቿንና አብያተ ክርስቲያናቷን በበለጠ አመራር ፈጽመው ከፍ ከፍ ያደርጉላት ዘንድ ትመኛለች።...”*

ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱንም መን ፈሳዊ ሥራና ሐዋርያዊ ተልእኮ በስፋት በመመልከት ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም ተገቢ ነው።

*ይሁን እንጂ ጵጵስና ለመንጋው እረኛ በመሆን የመጨረሻው መዐርገ ተክህኖ በመሆኑ ሓላፊነቱ አደራው ከባድ ነው። በዚህ የአባትነት ሹመት ደረጃ የሚፈለጉት ኤጲስ ቆጶሳት በሕገ ቤተ ክርስቲያን ምዕራፍ አምስት አንቀጽ ዐሥራ ስምንት ላይ በተደነ ገገው መሠረት መሆን አለበት። ይኸ ውም፦ ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም አስፈላጊ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲታመ ንበትና ሲወሰን፣ በሥርዐተ ምንኩስና በድንግልና መንኩሰው ቤተ ክርስቲያን ከሚያገለግሉና ለኤጲስ ቆጶስነት ብቁ ከሆኑት ቆሞሳት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ዕጩ ሆኖ ሲቀርብ፣ ኤጲስ ቆጶስ በሚመረጥበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሠየም አስመራጭ ኮሚቴ ተጠቁመው የሚቀርቡ ሲሆኑ ነው። /ሕገ ቤተ ክርስቲያን፣ ፲፱፻፺፩፣ ፲፪/*

በዚህም መሠረት በእጩ ምልመላ ወቅት ትምህርትና የአገልግሎት ዘመን፣ በአገልግለት ዘመናቸው የአሳዩት ትጋት ትሩፋት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

## ፩. የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ምልመላ ላይ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭም በአሉት አህጉረ ስብከት የሚካሄ ደውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገል ግሎት፣ ሐዋርያዊ ተልእኮ በስፋትና በተሟላ ሁኔታ ለማዳረስ የብፁዓን አባቶችን ቁጥር መጨመር አስፈላጊ

## ፪. ማኅጠነ ልቡና /think thank/ ማቋቋም

ይህ ማለት በጥልቀትና በብስለት የተለያዩ የውሳኔ ሐሳቦችን ለቅዱስ ሲኖዶስ ለውሳኔ በሚያመች መልኩ የሚያቀርብ ቡድን ማቋቋምን የሚገ ልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱን ፖሊሲ በማውጣት እና ስትራቴጂ በመንደፍ የመምራት ሓላፊነቱንና አደራውን በብቃት ለመወጣት በሚያ ስችል ሁኔታ አለመደራጀቱ በውሳኔ አሰጣጥና አፈጻጸም የራሱ የሆነ አሉ ታዊ ጎንን አስከትሏል። በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተልእኮ ተግባራዊነት መከታተያና መገምገሚያ ሥርዐት ያለው ሆኖ እንዲገኝ አላስቻለውም።

ስለዚህ በዋና ዋና የሥራ ዘርፎች ላይ /የፖሊሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የሃይማኖት፣ የሕግ ወዘተ/ ጉዳይ የሚያማክሩ የባለሞያ አማካሪ ቡድኖች /ማኅጠነ ልቡናን/ በማደራጀት ለሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር አካላት በአገል ጋይነት መንፈስ የሚሰጥበት አሠራር መዘርጋት ይኖርበታል።

## ፫. ተገቢውን አደረጃጀት ተግባራዊ ማድረግ

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒ ቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት ፈትሾ መሠረታዊ ተልእኮዋን ለማስፈጸም የሚያስችል፣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በአገናዘበ እና ከሥራዎቹ ስፋትና ውስብስብነት አንጻር ቀልጣፋ አሠራ ርን ሊያሰፍን በሚያስችል መልኩ ራሱን ማደራጀት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ራሱን ከዝርዝር ጉዳዮች እየለየ የቤተ ክርስቲያኒቱ ርእይ እና ዋና ዋና ዓላማዎችና ግቦች ላይ ማተኰር ይኖርበታል።

### ማጠቃለያ

የተቀደሰችውን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን አክብሮ የመሠረታት ባለቤቱ ኢየሱሱ ክርስቶስ ነው። ይህቺን ቤተ ክርስቲያን የመጠበቁንና የማስጠበቁን ሓላፊነት ደግሞ የሰጠው ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ቤተ ክርስ ቲያን የማትነጥፍ መንፈሳዊት ጥገት ሁና ከምታፈሰው መንፈሳዊ ሐሊብ ምእመናቿ እንዲጠቀሙ የቅዱስ ሲ ኖዶስ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ልዕልና መከበር ወሳኝ ነው። ቤተ ክርስቲ ያንም የቅድስና ዘውዷንና የክብር አክሊሏን ከራሷ ሳታወርድ መኖርዋ እንዲቀጥል የልዕልና ሲኖዶስ መገለጫ የሆኑት ውሳኔዎቹ መከበር አለባቸው።

የቤተ ክስቲያኒቱ አንድነት ተጠብቆ መከፋፈል እንዲጠፋ፣ ሕግ እና ሥርዐ ትም እንዲከበር፣ ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎችም መፍትሔዎች በቅዱስ ሲኖዶስ ቶሎ ተግባራዊ ቢሆኑ፤ ነገን ዛሬ መቅደም እንችላለን።

✞

# በእንተ ጦማረ ሐሰት. . .

ከገጽ ፲ የዞረ።

### *ማኅበሩ ማኅበሩን ሲቃወም*

በዕቅዳቸው ውስጥ ማኅበረ ቅዱሳን የሚያሳትማቸውን ኅትመቶች ያለ ኤዲቶሪያል ቦርድ ኅትመት አከናውኖ ማሠራጨት የሚል የተጠላለፈ አሳብ አስቀምጧል። በመሠረቱ ማኅበረ ቅዱሳን በመዋቅሩ እንዳመለከተው ማንኛውንም ኅትመት ኤዲቶሪያል ቦርዱ ዓይቶት ሲፈቅደው ይታተማል። ታዲያ እንዴት አንድ ማኅበር የራሱን መዋቅር እየጣሰ ለመሥራት ያቅዳል? አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ቦርዱን ማፍረስ ሲችል እንዴት ስለመጣስ ያስባል? እንዲህ ያለ ዕቅድ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅምና ዕቅድ አውጪዎቹ በጣም የተራቀቁ መሆን አለባቸው።

### *ዕቅዳቸውን ለራሳቸው ጥብቅና ሲያቆሙት*

ቅድስቲቱን እምነት ለመበረዝ የተነሡ የተሐድሶ ኦርቶዶክስ ዓላማ አራማጆች ስውር ተልእኮአቸው በአሁኑ ወቅት ስለተነቃባቸው ከገቡበት አዙሪት ለመውጣት ሲፍጨረጨሩ ይታያሉ። ከዚህም መንገድ አንዱ ተሐድሶ የሚባል የለም የሚል መፈከራቸውን ማስተጋባት ነው። ዕቅድ ተብየውም ይህንኑ የተከተለ ሳያውቀው በስውር ዓላማቸው የተቃኘ የተነረተ የበሽታ ሆድ ሆኖባቸዋል። ስለሆነም ከዕቅዱ መካከል በአንዱ ላይ ታላላቅ የቤተክ ርስቲያን መሪዎችና ተሐድሶዎች / ፖሉቲከኞች / ናቸው በማለት ከምእመኑ ሰላማዊ ቅብብል እነዳይኖራቸው የሚል ይገኛል /ቃላቱ እነርሱ እንዳስቀ መጧቸው የተቀመጡ ናቸው/።

በዚህ ዕቅድ ላይ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን ማስተዋል እንችላለን። አንደኛው ተሐድሶን ከፖለቲከኛነት ጋር ለመቀላቀል መታሰቡ ሲሆን ሁለተኛው ግን ታላላቅ የቤተክርስቲያን መሪዎች ያሏቸውን የሚመለከት ነው።

ተሐድሶ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲየንን ሙሉ በሙሉ ወደ ፕሮቴስታንት ጐራ ለመክተት አቅዶ የሚሠራ ሲሆን ፖለቲካኛ ደግሞ ሌላ ለዕቅድ አዘጋጆች ግን ተሐድሶ እና ፖለቲካ ተቀላቅሎባቸዋል። እውን ተቀላቅሎባቸው ይሆንን? መልሱ ለአንባቢው የሚተው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ታላላቅ የቤተክ ርስቲያኗ መሪዎችን ማኅበረ ቅዱሳን ስማቸውን እንደሚያጠፋ ያመላክ ታል። ታላላቆችማ ታላላቆች ናቸው። እነርሱን የሚቃወም ማንነቱ ግልጽ ነው። ስም ማጥፋትም ወንጀል ነው። ማኅበረ ቅዱሳን ግን ተሐድሶ የሆኑትን ተሐድሶ ናችሁ ከማለት አያፈ ገፍግም። ይህንን ሲያደርገ በማስረጃ እንጂ በተራ አሉቧልታ አይደለም። ነገር ግን ታላላቆችን አባቶች የሚነኩትን ማኅበሩም ዝም አይላቸውም ተልእ ኳቸው ይታወቃልና። ይሁን እንጂ ሊያስተላልፉ የፈለጉት ተሐድሶ የለም የሚለውን የዘወትር የጨለማ መጋረ ጃቸውን ለመሆኑ ማን ሁለት ጊዜ ያስባል? ድንጋይ ይቧጥጣሉ እንጂ መጋለጣቸው አይቀርም። ይህ ሁሉ የሐሰት ደበሎ ይገለጣል።

### *የጽንሰ ሐሳብ ችግር*

ከዝርዝር ዕቅዳቸው አንዱ ባልተ ጠኑ ትምህርቶች የቤተርክስቲያኗን ምእመናን ደጋፊ ማድረግ ይላል። አንድ ጤናማ እና የሚያስብ አእምሮ ያለው ሰው ይህንን አባባል እንዴት ይረዳዋል? ብሎ መገመት እጅግ ቀላል ይሆናል። ዕቅድ እያቀደ ያለ አንድ አካል እንዴት ባልተጠና ትምህርት ሌላውን ሊያሳምን ይችላል? ዕቅዱን ያቀዱት ሰዎች የሰለቻቸው ይመስላል። ማኅበረ ቅዱሳን የግቢ ጉባኤያት / የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ተማሪ ዎችን/ የሚያስተምረው በተጠና ሥርዐተ ትምህርት መሆኑን እያወቁ እንዴት ይህን ሊሉ ቻሉ? በእርግጥም ደክሟቸው መሆን አለበት።

### *የጽሑፉ ዓላማ*

ማኅበረ ቅዱሳን ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ማኅበራት እና ልጆች ጋር በመቀናጀት በአሁኑ ሰዓት ፀረ ተሐድሶ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በዚህም ምክንያት ማዕበሉ እያንገለለ እየለያቸው ያሉ የተደራጁ የሃይማኖት ጠላቶች ማምለጫ እስኪያጡ ድረስ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል። የተዋሕዶ ምእመናንን እየሰለቿቸው መጥተዋል። በመሽማቀቅ በቁማቸው አልቀዋል። ከመጠን በላይ በመደን ገጣቸው ምክንያት ሳያስቡት የመጣባ ቸውን እውነት ለመጋፈጥ የሚያስችል መንፈሳዊ ተክለ ሰውነት አጠተዋል። ስለሆነም አቋራጭ የመሰላቸው የጨከነፈ ስልት ነድፈዋል። በዋነኛነትም የሞት ሽረት ትግል ለማድረግ አስበዋል። በዚህም መንገዳቸው አንዱ የማኅበሩን ስም በድብቅ ሆኖ ማጥፋት ነው።

እውነተኞች ሰዎች ከሆኑ ማንነ ታቸውን ገልጠው ፊት ለፊት በያዙት መረጃ በታገሉ ነበር። ለዚህ ያልታደሉ የመልካም ዘር ፀሮች በመሆናቸው መደበቁን መርጠዋል። ተደብቆ ውጭ ማኅበረ ቅዱሳን ሊያስበው ከቶውኑ የማይፈልገውን ያስቡለታል። "አዛኝ ቅቤ አንጓች" እንደሚባለው ሆኖባቸው በዚህ ስልት ማኅበሩን ለማጥቃት ሞክረዋል ራሳቸው ጽፈው ሊሰሙን ይችላሉ ብለው ለሚያስቧቸው አካላት ጽሑፉን ለመበተን መክረዋል፤ ይህንን ማድረጋቸውም አንድም አባቶ ችን ንቀዋቸዋል አለበለዚያም ተዳፍ ረዋል።

ይህንን ከደረጃ ወጥቶ ጊዜ ወስዶ የተንኮታኮተ ጽሑፍ ዕቅድ ብለው ይዘው መዞራቸው በትክክል ማንነታ ቸውን ይገልጥባቸዋል። በየትኛውም መመዘኛ ማኅበረ ቅዱሳንን የማይመስል ወዘና የሌለው ወረቀት ብቅ ማድረግ ማንነታቸውን ገልጠዋል። በዝምታ ሊታለፉ አይገባቸውም።

### *ማጠቃለያ*

ይህንን ጽሑፍ ያሰራጩት አካለት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ማንም ሰው መገመት ይችላል። ከመገመትም አልፎ አገኘሁ ብሎ ማኅበሩን ለማጥላላት የሚጠቀምበት ሁሉ እንዳለ ይታወ ቃል። ተቀባዮችም የሰጪዎችን ማንነት ያውቃሉ። እንዲያውም ከማብራሪያ ጋር እንደተቀበሉ ይታመናል ።

### *ስለሆነም፦*

፩. ይህ የሐሰት ጽሑፍ የደረሳቸው አካላት ሰዎችን በማጋለጥ ሊተባበሩ ይገባል፤

፪. ማኅበሩ እነዚህን አካላት በሕግ መጠየቅ ይፈልጋል። ስለሆነም ቅዱስ ሲናዶስ የእነዚህን ሰዎች ማንነት አጣርቶ ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጥን እንፈልጋለን፤

፫. ይህ ጽሑፉ የደረሳቸው ምእመናን በሐሰተ ሥራ እንዳይታለሉ እናሳስ ባለን። አስፈላጊ ሆኖ ካገኙትም ወደ ማኅበሩ ጽ/ቤት በመምጣት ተገቢውን ውይይት ማድረግ እንደ ሚችሉ እንጠቁማለን።

✞

ስምዐ ጽድቅ
ጋዜጣን
እና
ሐመር መጽሔትን
በማንበብ ነፍስዎን
ቃለ እግዚአብሔር
ይመግቡ!

# የቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ልዕልና

*"… ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ እየተሾሙ የመጡ ግብጻውያን ጳጳሳት ብዙዎች ናቸው። ቁጥራቸውም ከአቡነ ሰላማ እስከ አቡነ ቄርሎስ አንድ መቶ ዐሥራ ሦስት ናቸው። የዘመናቸውም ቁጥር ሺሕ ከ፮ መቶ፲፫ት መሆኑ ነው። እነዚህን እያንዳንዳቸው የሹመታቸው ማዕረግ እንዲህ ትላቸው ነበር። በሊቃነ ጳጳሳት ስም ብቻ ያክብሩት፣ የዚህ ሥልጣን ለርሱ ሳይገባው /ሳይሰጠው/ እያለች ትልካቸው ነበረች። ስም ተሰጥተው የሥልጣኑ ሥራ ተከልክለው ነበርና። እነዚህ ሁሉ ይህን ማዕረግ አልተቀበሉም። እንግዲህ እንደ ብፁዕነትዎ ያለ ዕደለኛ ማነው? እንደ ብፁዕነትዎስ በረከትን የሚሰጥ ከኃይል ወደ ኃይል ማለት ከትሩፋት ወደ ትሩፋት የሚሔድ፣ ከማዕረግ ወደ ማዕረግ የሚራመድ መምህረ ሕግ ማነው? እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሹመትን ተቀብለው ለዘለዓለም ለኢትዮጵያ የክህነት መሠረተ ብፁዕነትዎ ነዎትና። የደብረ ሊባኖስ ዕጨጌዎችና የኢትዮጵያ ሊቃነ ካህናት የሆኑ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት ሐዲስ ሐዋርያ ከተባሉት ከኢትዮጵያ ፀሐይ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጀምሮ እስከ ብፁዕነትዎ ያሉት ቁጥራቸው ስልሳ ሲሆኑ ዘመናቸውም ሰባት መቶ ያህል ሆኗል። እነዚህ ሁሉ ይህን ሰማያዊ ሀብተ ጸጋ፣ ይህን መንፈሳዊ ማዕረገ ተክህኖ አላገኙትም፤ በስምንተኛው ሺሕ የተነሡት ይቅሩና ቀደም ብለው የተነሡት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ዐሥራ ሁለቱ የኢትዮጵያ ኖሎት ፊልጶስና አኖሬዎስ፣ አድኀኒና ኢየሱስ፣ ማትያስና ዮሴፍ፣ ታዴዎስና ገብረ ክርስቶስ፣ ቀውስጦስና ሳሙኤል፣ መርቆሬዎስና አኖሬዎስ እሊህ ብሩሃን ከዋክብትና የቀሩትም የኢትዮጵያ ቅዱሳን ይህቺን የማዕረግ ተክህኖ ስም አላገኙዎትም።*

*እንዲሁም የደብረ ብስራቱ አባታችን ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ብሔረ አግዓዚን በትምህርታቸው ብርሃንነት ያበሯት፤ በገድል ትሩፋትና በክብረ ጸጋ በአባትነታቸው ከብፁዕነትዎ በላይ ሲሆኑ ይህችን የክህነት አገልግሎት ሹመት ማዕረግ አላገኙዋትም።*

*ልጃቸው የሚሆኑ ብፁዕነትዎ ዛሬ እንደተቀበሉት ያለ ማዕረግ ከተቀበለው ከእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ብንያሚ በረከት /ቡራኬ/ ለመቀበል ወደ ግብጽ ወርደው ነበር እንጂ። ይልቁንም የአቡነ ዜና ማርቆስ የሥጋ ወንድም ታላቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሰማያዊት ልዕልና ደግሞ በአባትነታቸው ከብፁነትዎ በላይ ያሉት የኢትዮጵያ ሊቀ ካህናት ጳጳሳት ሆነው ሳሉ፤ ይህቺን የማዕረግ ስም አልወሰዷትም። እድለኛው ልጃቸው ብፁዕ አባታችን ዛሬ እጅ አድርገዋት የምናያትን ማዕረግ ከዚያ ከፓትርያርኩ ከአባ ብንያሚ በረከተ እድ ለመቀበል ወደ ግብጽ ወረዱ እንጂ። ብፁዕ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነው ከመንፈሳዊት ኢትዮጵያ ከወለድዋቸው ልጆች መንፈሳውያን ሁሉ እንደብፁዕነትዎ ዕድለኛ ሆኖ የመንፈሳዊ ሹመት ፍጻሜ ክብርን የተቀበለ እና በዚህ በፓትርያርክነት ስም የተሠየመ የለም።*

*ይህም ነገር ለኢትዮጵያ እጅግ ፈጽሞ ሐዲስ ነገር ነው። እንግዲህ ይህን ሁሉ ላደረግልዎ ለልዑል እግዚአብሔር ምን ዋጋ ይከፍሉት ይሆን? ኢትዮጵያ ካለፈው ይልቅ ለሚመጣው ተስፋ ታደርግዎታለች። ይህን አይታው የማታውቀውን ማዕረገ ተክህኖ ለማስገኘት ዕድልዎ ምክንያት ሆኖ እንዳስገኙላት እንደዚሁም በአባትነትዎ ጸሎትና በመንፈሳዊ መሪነትዎ መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶቿንና አብያተ ክርስቲያናቷን በበለጠ አመራር ፈጽመው ከፍ ከፍ ያደርጉላት ዘንድ ትመኛለች።…" /ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣ፣ ፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩ ሐምሌ ፲፱፻፵፩ ዓ.ም/*

ከዛሬ ሃምሳ ሁለት ዓመት /ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ.ም./ በፊት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በዓለ ሢመት ላይ ተገኝተው ይህን ታሪካዊ ንግግር ያደረጉት መምህር ተከሥተ ብርሃን ወልደ ኢየሱስ ናቸው።

መምህር ተከሥተ ብርሃን ወልደ ኢየሱስ የሢመተ ፓትርክና ታላቅነት እና ቅድስና፤ በቅድስናም፣ በአባትነትም ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የሚበልጡት ቅዱሳን አበው ኢትዮጵያውያን ያላገኙት ማዕረግ ተክህኖ ማግኘታቸው ከቤተ ክርስቲያን አልፋ ለአገሪቱ ኩራት መሆኑንን የገለፁበት ንግግራቸው ነው።

ይህ ንግግር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን የአንድ ሺሕ ስድስት መቶ ዘመን ጥገኝነት እና ከብዙ ዘመናት ውጣ ውረድና እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ በራሷ ልጆች የራሷን ሲኖዶስ አቋቁማ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባቷንም ያበሰረ ነው።

ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ እንዲሁም እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የቤተ ክርስቲያን መሪ

**ቤተ ክርስቲያን የማትነጥፍ መንፈሳዊት ጥገት ሁና ከምታፈሰው መንፈሳዊ ሐሊብ ምእመናኗ እንዲጠቀሙ የቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ልዕልና መከበር ወሳኝ ነው:: ቤተ ክርስቲያንም የቅድስና ዘውዷንና የክብር አክሊሏን ከራሷ ሳታወርድ መኖርዋ እንዲቀጥል የልዕልና ሲኖዶስ መገለጫ የሆኑት ውሳኔዎቹ መከበር አለባቸው::**

ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ሰማያዊ አገልግሎቷንም ስታካሒድ የኖረችውም በመንፈስ ቅዱስ በሚመራው በቅዱስ ሲኖዶስ በመመራት ነው።

"በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሲኖዶስ ደግሞ የራሱ የሆነ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ልዕልና አለው። ይኸንንም ሕገ ቤተ ክርስቲያን በምዕራፍ ሁለት አንቀጽ አምስት ላይ እንዲህ ብሏል።

*በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስተያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት ነው። ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን መዋቅር ሁሉ የበላይ አካል ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ሕጎችን፣ ልዩ ልዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የዳኝነት ሥልጣን አለው።» /ሕገ ቤተ ክርስቲያ፣ ፲፱፻፺፩፣ ፫/*

እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ልዕልናን የተጉናጸፈ ሲኖዶስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ፣ አገልግሎቷንም የተሟላ እንዲሆን ለማድግ፣ ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳት፣ ጳጳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በዓመት ጥቅምት ፲፪ ቀን እና ትንሣኤ በዋለ በሃያ አስምተኛው ቀን /በርክበ ካህናት/ እንዲሁም ቅዱስ ፓትርያርኩ ወይም ቋሚ ሲኖዶስ በሚያደርጉት ጥሪ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ይካሔዳል። በእነዚህ ጉባኤዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች፣ የሚወጡ ደንቦችና ልዩ ልዩ መመሪያዎች፤ የሚደነገጉ ሕጐች ሁሉ ተግባራዊ የመሆን ግዴታ አለባቸው። ተግባራዊነታቸውም የቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ልዕልና መገለጫዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ልዕልና መገለጫ የሆኑትን ውሳኔዎቹን ለማስጠበቅ አለመቻሉን ብዙዎቹ ሊቃነ ጳጳት፤ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን የሚገልጡት ሐቅ ነው።

ለዚህም መነሻ የሚያደርጉት በተለያዩ ጊዜያት የወሰናቸውን ውሳኔዎች በማስታወስ ነው። በግንቦት ፳፻፩ ዓ.ም "በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚታየውን የአስተዳደር ችግር በጥልቀትና በስፋት የሚከታተልና መፍትሔ የሚሰጥ፣ ተጠሪነቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ የሆነ ኮሚቴ መሠየሙ ይታወሳል። የኮሚቴውም የሥራ ዘመን አንድ ዓመት ሆኖ "ሥራውን እየሠራ የመተዳደሪያ ደንብ አርቅቆ ለሐምሌ ምልዓተ ጉባኤ እንዲያቀርብ" ተወስኖ የነበረ ቢሆንም ውሳኔው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

እንዲሁም በሌላ ጊዜ "አጉራ ዘለል ሰባክያንን" በተመለከተ ያለ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ እንዳያስተምሩ የተወሰነ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የሚያፋልሱ ድርጊቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የተላለፈው ውሳኔ ተግባራዊ ሳይሆን ይኸው የግንቦቱ ርክበ ካህናት ምልዓተ ጉባኤ ስብሰባ ደረሰ። እነዚህን እንደ ቅርብ ጊዜ ማሳያዎች አቀረብን እንጂ በተለያዩ ጊዜያት ተወስነው ተግባራዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች መኖራቸውን አጥተን አይደለም።

ለውሳኔዎቹም አለመተግበር እንደ ምክንያት በብዙዎቹ ብፁዓን አበው

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል::

## በእንተ ርክበ ካህናት

የዚህ ጉባኤ መነሻው የቀደሙት መንፈሳውያን አባቶች ከበዓተ ክረምት አስቀድሞና ከፀዓተ ክረምት በኋላ ማለት ክርምት ከመግባቱ በፊት፤ ክረምት ከመውጣቱ በኋላ ጉባኤ አድርገው በመንፈሳዊው አገልግሎት ላይ ስለገጠማቸው ችግር ይነጋገሩ ነበርና ይህንኑ ሕገ አበው በማጽናት ነው::

የጉባኤ መክፈቻ ቀን የሆነው ርክበ ካህናትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ከሐዋርያት ጋር የተገናኘበት /ርክበ ካህናት/ ነው::

✞